# የአማራው ሕዝብ ሕልውና፣ አስተዋጽኦውና ከሌሎች ጎሣዎች ጋር ያለው ግንኙነት

ይህ ጥናት በአርእስቱ የተመለከተውን ጉዳይ በሚከተሉት ስድስት ክፍሎች በመዘርዘር ይተነትናል፣

1. ‹አማራ› ወይም ‹አምሐራ› የሚለው ቃል፣
2. የአማራው ሕዝብ ታሪክ ባጭሩ፣
3. አማራው ሕዝብና የኢትዮጵያ አንድነት፣
4. የአማራው የትምህርት አስተዋጽኦ፣
5. አማራውና ሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ግንኙነት፣
6. መደምደሚያ።

*From the Library of*

ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ

FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

## ማብራሪያ

- ተ.ጸ.መ.፥ ኢ.ታ... = ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ...
- ተ.ጸ.መ.፥ ግ.አ.ወ...= ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የግራኝ አሕመድ ወረራ...
- አ.ኪ.ወ. = አለቃ ኪዳነ ወልድ፥ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ
- ከ.ብ.ተ. = ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፥ የአማርኛ መዝገበ ቃላት
- ዓመተ ምሕረት፥ በተለይ እንደ አውሮጳውያን መሆኑ ካልተጠቀሰ በስተቀር፣ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።

# መቅድም

ባሁኑ ጊዜ ባገራችን የሚካሔደው ለውጥ ባስከተላቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የባሕል ውዝግቦች ምክንያት ፣ ብዙ ሰዎች ከመቼውም ይልቅ በልዩ ልዩ አገርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በጽሑፍና በቃል ሐሳብ እየተለዋወጡ ናቸው።

ከእርእሰቶቹ ውስጥ አንዱ፣ ‹አማራ› የሚባል ነገድ ወይም ጎሣ አለ ወይስ የለም? ካለስ ከየትና መቼስ መጣ? ዛሬስ የሚገኘው የት ነው? የሚል ሲሆን፣ ከተቺዎቹ አንዳንዶቹ ‹አማራ› የሚባል ሕዝብ የለም ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ አለ ነገር ግን ብዙ አማራ ከታሪካውያን የአማራ ክፍለ ሀገሮች ውጭ ሰፍሮ ስለሚገኝ ወካይ ለመምረጥ ያዳግታል፣ ባዮች ናቸው።

ለዚህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ለመስጠት ከመሞከሩ አስቀድሞ ‹አማራ› የሚለው ቃል ከየት እንደመጣና ዘይቤውም ምን እንደሆነ ከነማስረጃው በመጠኑ በጥናቱ አንደኛ ክፍል ይቀርባል።

በሁለተኛው ክፍል፣ ‹አማራ› የሚባል ሕዝብ ወይም ነገድ በኢትዮጵያ የነበረና፣ ያለ መሆኑ ከታሪክ አንጻር ባጭሩ ይገለጻል።

በሦስተኛው ክፍል ደግሞ፣ አማራው ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ጥበቃ በተለይም ኢትዮጵያን የመምራት ሐላፊነት ባሥራ ሁለተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ከዛጔዎች ከተረከበ በኋላ ያደረገውን ታላቅ ተጋድሎና መሥዋዕትነት የግራኝ አሕመድን ወረራ፣ የዐድዋን ጦርነትና የ1928 ዓ.ም. የኢጣልያ ያምስት ዓመት ወረራ መሠረት በማድረግ አስተዋጽኦውን ለመጠቆም ሙከራ ይደረጋል።

አማራው ሕዝብ በአስተዳደር፣ በትምህርትና በሥነ ጽሑፍ ረገድ ያደረገው አስተዋጽኦ በአራተኛው ክፍል ከተጠቀሰ በኋላ፣ የአማራውና የሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ወይም ነገዶች ግንኙነት ባጭሩ በአምስተኛው ክፍል ይገለጻል።

በዚሁ ክፍል አማራው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ፍጹም አካል እንደመሆኑ መጠን ስለ ኢትዮጵያ አንድነት፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ትክክለኛ አስተዳደር በሚደረገው ጥረት ሁሉ ሙሉ ተሳታፊነት እንደነበረውና ሊኖረውም እንደሚገባ አስተያየት ይሰነዘራል።



የጥናቱ መደምደሚያ፣ ‹አማራ› የሚባል ሕዝብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር መሆኑን፣ ተረት (Mythos) አለመሆኑን ወይም ከዚህ ዓለም ውጭ ያለና በአእምሮ ጥልቀት ብቻ የሚለካ (Metaphysics) አለመሆኑን፣ ለማስረዳት ይጥራል።

በዚህም መሠረት፣ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል በሚደረገው ማናቸውም እርምጃና ውሳኔ፣ አማራው እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ መሳተፍና ተገቢ ድርሻውን ማበርከት ሕጋዊ መብቱና ግዴታው ስለሆነ፣ ለማስከበር ምንጊዜም ዝግጁ ነው።

ይህ ጥናት የተዘጋጀው፣ የኢትዮጵያን አንድነትና የሕዝቧንም እኩልነት፣ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት መሠረት በማድረግ ስለሆነ፣ የአማራውን ሕዝብ ሕልውናና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተጫወተውን ሚና ለመጠቆም እንጂ ለይቶ ለማሞገስ በምንም ዓይነት በጐሣ ተለይቶ እንዲደራጅ ለማበረታት የታቀደ አለመሆኑ ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል።

ጥናቱ የተዘጋጀው በተለይ በውጪ አገርና በአገር ቤት ለሚገኙት የአገራችን የወደፊት ተስፋና አለኝታ ለሆኑት ወጣቶች ስለሆነ፣ ዐረፍተ ነገሮቹ በሐረግ ሳይጠላለፉ አጫጭሮች ናቸው። ይህም ፍሬ ነገሩን በቀላሉ ለመረዳት እንደሚያስችላቸው ተስፋ ተጥሎበታል።

# ክፍል አንድ

## ‹አማራ› ወይም ‹አምሐራ› ስለሚባለው ቃል

ነገደ ዮቅጣን ወይም ነገደ አግአዝያን የሚባሉት የጥንት ኢትዮጵያውያን አባቶች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ከቅርብ ምሥራቅ ሲሆን፣ እነሱም ሳባ፣ ሀበሳና ሆሚሪት ወይም ሂሚያሪት ይባላሉ። ሳባ፣ ሀበሳና ሆሚሪት ወይም ሂሚያሪት የነገድ ስሞች ናቸው። ሆሚሪት ወይም ሂሚሪያት የሚባለው በጊዜ ብዛት ፊደሉ ቢለወጥም ‹አማራ› ማለት እንደሆነ ብዙ የቋንቋና የታሪክ ሊቃውንት ይገምታሉ። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ. ገጽ 8) በከሣቴ ብርሃን ተሰማ መሠረት ዐምሐራም ማለት ነፃነት ያለው ሕዝብ፣ ጌታ፣ ባላባት፣ የሰው ልጅ፣ ጨዋ ማለት ነው። (ከ.ብ.ተ.፣ ገጽ 14)

‹አማራ› ወይም ‹አምሐራ› ለሚባለው ቃል የእብራይስጡ ‹አም፣ ሐ-አሬዝ› በጣም ይቀርባል። ቅርበቱም በአነጋገር ብቻ ሳይሆን በትርጉምም ጥምር ነው። እብራይስጥ፣ ዓረብኛና ግዕዝ ከደቡባዊ የሴም ቋንቋዎች የፈለቁና ተመሳሳይነታቸውም የተመሠረተው በዚህ ላይ ስለሆነ፣ እምብዛም አያስደንቅም።

ሆኖም ምንም እንኳን ምስቱ ሴማውያን ቋንቋዎች የወል ምንጭ ቢኖራቸው በፊደል ቅርጽና በአጻጻፍ ስልት አይገናኙም (የተለያዩ ናቸው)። ዓረብኛና ዕብራይስጥ ከቀኝ ወደ ግራ ሲጻፉ ግዕዝ እንዲሁም ከሱ የተገኙት አማርኛና ትግርኛ ከግራ ወደ ቀኝ ይጻፋሉ። በጥንት ጊዜ የጽሕፈት ሥነ ሥርዓት የሚያርሱ በሮችን ሒደት (በግሪክኛ Boustrophedon ይባላል) ይመስል ነበር፣ ማለት ከግራ ወይም ከቀኝ ተጀምሮ ብራናው ወይም ወረቀቱ እስኪያልቅ ድረስ ከአንዱ ጽንፍ ወደሌላው እየተዘዋወሩ መጻፍ ነበር።

‹አማራ› ወይም ‹አምሐራ› የሚለው ቃል ከየት እንደመጣ ባጭሩ ከጠቀስን በኋላ ዘይቤው ምን እንደሆነ እንመርምር። ቃሉ ከእብራይስጡ ቃል ጋር በጣም የተቀራረበ ስለሆነ ምርምራችን በእብራይስጥ ስነ ጽሑፍ በተለይም በብሉይ ኪዳን ላይ ያተኩራል።

‹አማራ› የሚለው ቃል በእብራይስጥ ‹አም፣ ሐ-አሬዝ› እንደሚባል ቀደም ብሎ ተጠቅሷል። የቁም ወይም የቃል በቃል ትርጉሙ አም፣ ሕዝብ፣ ሐ-አሬዝ አንድ የተወሰነ ቦታ ወይም አገር፣ ባጠቃላይ የአንድ የተወሰነ ሀገር ነዋሪ ወይም



ባለ-ሀገር ሕዝብ ማለት ነው። ለምሳሌ ሕዝበ እስራኤል፣ ሕዝበ ኢትዮጵያ። በብሉይ ኪዳን እብራይስጥ የቃሉ ትርጉም አንዳንድ ጊዜ እንደ ዐረፍተ ነገሩ አገባብ የተለየ ትርጉም ቢኖረውም፣ አብዛኛውን ጊዜ እስራኤላዊ ወይም የሌላ አገር (ባዕድ) ሕዝብ ማለት ነው።

<u>ማስረጃዎች</u>

(i) ቃሉ ‹ሕዝበ እስራኤል› የሚል ትርጉም ሲኖረው፣ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 16:15 እና 25:3፤ ሕዝቅኤል 39:13 እና 45:22፤

(ii) እስራኤላዊ ያልሆነ ሕዝብን ሲያመለክት፣ ዘፍጥረት 42:6 (ግብፅ)፤ ኍልቊ 14:9 (ከነዓን)፤ እዝራ 4:4

በቁጥር (i) እና (ii) የተሰጠው ትርጉም ቃሉ በነጠላው ሲተረጎም ነው። ቃሉ በብዙ (plural) አጥቅም ላይ ሲውል (አምሐራቾት = አሕዛብ) እንደ ግዕዙ ‹አሕዛብ› ማለት ነው። በባሕልም ሆነ በሃይማኖት የተለየ ባዕድ ሕዝብን ያመለክታል፣ (Encyclopaedia Judaica vol. 2, p.833-836 4th Ed, 1978.)

በግዕዝ ‹አምሐራ› ወይም ‹ቤተ አምሐራ›፣ በአማርኛ ደግሞ ‹አማራ› የሚባሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከደቡብ ዓረብ ቀይ ባሕርን ተሻግረው ዛሬ ‹አማራ ሳይንት› በሚባለው ሥፍራ የሰፈሩትን ነገደ ዮቅጣን ወይም ነገደ አግአዝያን ነው። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 8)።

የነገደ አግአዝያን ቋንቋ በመጀመሪያ ግዕዝ ሲሆን፣ በኋላ አማርኛ የሚባለውን ቅርንጫፍ አስገኘ፣ ላቲን ፈረንሳይኛን፣ ኢጣልያንኛንና ፖርቱጊዝኛን እንዳስገኘ ሁሉ። አማርኛም የመንግሥት ሥልጣን ከዟጒዎች ወደ አማሮች ሲዛወር ዋና የኢትዮጵያውያን መገናኛና ሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ሆነ።

‹አማራ› ወይም ‹አምሐራ› የሚለው ቃል አመጣጥና ዘይቤ ባጭሩ ይህ ሲሆን፣ እስቲ የ‹አማራ›ን ታሪክ እንመልከት።

# ክፍል ሁለት

## የአማራ ታሪክ ባጭሩ

በዘመኑ ርቀት ምክንያት በጊዜው የተጻፈ ታሪክ ባለመኖሩ ዛሬ ያማራን ታሪክ መጻፍ አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ያገራችንን የቀድሞ ሊቃውንት አስተያየት ከአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር በማነጻጸር ከሞላ ጎደል ይህ ክፍል ሁለት ተዘጋጅቷል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከቅርብ ምሥራቅ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ቀይ ባሕርን አቋርጠው የተሻገሩት ሕዝቦች ነገደ ዮቅጣን ወይም ነገደ አግአዝያን ይባሉ ነበር።

ነገደ ዮቅጣን የሴም የልጅ ልጆች ናቸው። ከሴም 3ኛ ልጅ ከአርፋክሳድ (ሴም-- አርፋክሳድ-- ቃይናን-- ሳላ-- ኤቦር-- ዮቅጣን) የልጅ ልጅ ከኤቦር ይወለዳሉ። (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ. 10 ቁ. 25-29፤ አለቃ ታየ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፤ ገጽ 37)

ዮቅጣን 13 ልጆች ወልዷል። በአለቃ ታየ መጽሐፍ መሠረት ከነዚህ ከ13ቱ የዮቅጣን ልጆች 5ቱ ሳባ፤ ኦፊር፤ ሐዊላ፤ ኢባል እና አቢማኤል የሚባሉት ቦታ በጠበባቸው ጊዜ ከእስያ ተነስተው ብዙ ሠራዊት ሆነው ሲፈልሱ፤ ሲሄዱ ሲጓዙ ደቡብ ዓረብ ደረሱ። በዚያን ጊዜ፤ ምንም በፖለቲካ ምክር ባይስማሙም ለኩሳ የመን ይገብሩ ነበር። በኋላ ግን የሱን ደካማነት አይተው፤ በተንኮልም በሌላ ጥበብም ሕዝቡን እርስ በርሱ አሸፍተው ከወገናቸው ያርባ የሚባል ብልሀተኛ ጀግና አንግሠው ለደቡብ ዓረብ ሁሉ ባለቤቶች ሆኑ። ከነዚህ ነገድ በነገደ ካም መንግሥት መጨረሻ በኢአሪ፤ 1ኛ ዘመን በ3510 ዓመተ ዓለም አግአዝያን ተባሉ። አግአዝያን ከደቡብ ዓረብ ተነሥተው በባብ እልመንደብ ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ኢትዮጵያ የሚባለውም ስም ኢትዮጲስ ከሚባለው የሳባ የልጅ ልጅ (ዮቅጣን-- ሳባ-- ቡልቅያ-- ኢትዮጲስ) እንደተገኘ አለቃ ታየ ያትታሉ። (አለቃ ታየ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፤ ገጽ 38)

አለቃ ኪዳነ ወልድ ኢትዮጲስ የኩሽ ትርጉም ነው በማለት ከአለቃ ታየ አስተያየት ይለያሉ። እንደሳቸው አስተያየት ኢትዮጲስ ወይም ኩሽ የሚለው ቃል የሀገር ስም ሲሆን ‹ቀላ በረሐ ምድረ በዳ ስለ ኾነ› በረሓነት ላለው



ለእስያም ክፍል ለቃዴስ ባርኔና ለሐቅለ ሲና ይነገራል።› (አ.ኪ ወ.፤ ገጽ 13)

ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ጎሣዎች ነገደ ዮቅጣን የሚባሉት በነገዳቸው፤ አግአዝያን ደግሞ በነፃ አውጭነታቸው የሚጠሩበት ስም ነው። በኤና ሊትማንና በኮንቲ ሮሲኒ ጥናት መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የተሻገሩት ነገደ አግአዝያን በደቡብ ዓረብ ከቀሩት ነገዶች ጋር የቋንቋና የባሕል ዝምድና እንዲሁም የአምልኮ ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል። አምልኮታቸውም እስራኤሎች የሚያመልኩት አንድ አምላክ - ያሕዌ፤ ጆሆቫ ወይም አዶናይ - ሳይሆን ማኅረም የሚባለው የጨረቃና የከዋክብት አምላክ ነበር። በቋንቋም ረገድ ነገደ ዮቅጣን በሳባ፤ በግዕዝና በዚያን ዘመን የዓለም መገናኛ ቋንቋ በነበረው በግሪክ ሲጽፉ (ሲጠቀሙ) በተደረገው ጥናት መሠረት የእብራይስጥ ጽሑፍ አልተገኘም።

እስቲ እነዚህ የዮቅጣን ነገዶች እነማን እንደነበሩና በየት-በየት እንደሰፈሩም ጠለቅ አድርገን እንመልከት። ይህንንም በማድረግ ለተነሳንበት ዓላማ አማራ የሚባል ነገድ ነበረ (አለ) ወይስ አልነበረም (የለም) ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ያስችለን ይሆናል።

በደቡብ ዓረብ በኩል ከክርስቶስ ልደት በፊት ቀይ ባሕርን ተሻግረው፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ተሰራጭተው የተቀመጡትን ነገዶች የግዕዙ ታሪክ ነገሥት ነገደ ዮቅጣን ይላቸዋል። ኖህ ለአዳም አሥረኛ ትውልድ ሲሆን፤ ዮቅጣን ደግሞ ለኖህ ልጅ ለሴም አራተኛ ትውልድ ነው። በሌላ አነጋገር ከአዳም እስከ ዮቅጣን 15 ትውልድ መሆኑ ነው። (ከአዳም እስከ ኖህ አሥር ትውልድ፤ ከኖህ እስከ ሴም አንድ ትውልድ፤ ከሴም እስከ ዮቅጣን አራት ትውልድ በጠቅላላው አሥራ አምስት ትውልድ)። ይህ አስተሳሰብ የተመሠረተው በብሉይ ኪዳን ትምህርት ላይ እንጂ በሳይንስ አይደለም።

ስለዚህ ከደቡብ ዓረብ ወደ ኢትዮጵያ የተሻገሩት ነገዶች በሴም ሴማውያን፤ በዮቅጣን ደግሞ ነገደ ዮቅጣን ይባላሉ ማለት ነው።

እነዚህ ከልዩ ልዩ የሴም ነገድ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የሳባ፤ የሀበሳን፤ የሂሚያሪት፤ ጎሣዎች ለትግሬ፤ ለትግራይና ለአማራ ሕዝብ የነገድ ግንድ ወይም አባት መሆናቸው ቢታወቅም በዘመኑ ርቀትና በነገዶቹ ቅርንጫፍ ብዛት

ምክንያት በእርግጥ እገሌ ነገድ የእገሌ አባት ነው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል። ሆኖም ያን ጊዜ ሀበሳት የሚባለው ዛሬ ሀበሻ የሚባለው መሆኑን ለመገመት አያዳግትም። በተጨማሪ አፈር የአፋር (አዳል)፣ ኢባል ደግሞ የውጋዴን ሱማሌ የነገድ አባቶች እንደሆኑ ይገመታል። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 1ኛ መጽሐፍ፣ ገጽ 231)

የኢትዮጵያንና የደቡብ ዓረብን ገጸ ምድር (ጂኦግራፊ) አቀማመጥ ስንመለከት፣ በደቡብ ዓረብ በስተ ምዕራብ በኩል ፊት ለፊት የሚታየው የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ነው። ስለዚህ፣ ሀ) የሳባ ወገኖች በሐማሴን፣ በአኮለ ጉዛይ፣ በእጋሜ፣ ለ) የሀበሳን ወገኖች በአባሆርታ፣ በሐውዜን፣ ሐ) ሂሚያሪትና ሆሚሪት ሳባና ሀበሳን ከሰፈሩበት በስተደቡብ በኩል ያለውን ሰፋፊ አውራጃ ይዘው ስለሰፈሩ፣ ሂሚያሪት ወይም ሆሚሪት የሚለው ስያሜ በጊዜ ብዛት ትንሽ ፊደሉንና አነጋገሩን እየለወጠ መጥቶ በሂሚያሪት አምሐራ ተብሉ ይሆናል። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 8)

ሂሚያሪት ወይም ሆሚሪት ከሚለው አነጋገር የእብራይስጡ ቃል - አም ሐሬዝ - ለግዕዙና ለአማርኛው ቅርብ መሆኑ ከፍ ብሎ በተሰጠው ዘይቤ ቃል ተመልክቷል።

ስለዚህ፣ የአማራው ሕዝብ የመጀመሪያው መሠረታዊ አገር አምሐራ-ሳይንትና ቤተ አምሐራ የሚገኝበት ሐይቅ ደብረ እስጢፋኖስ፣ ግሸን መካነ ነገሥት፣ እነ ተድባበ ማርያም፣ እነ አትሮንስ ማርያም፣ የሚገኙበት ታላቅና ለምለም አውራጃ ነው። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 8) ዋናዎቹ የአማራ አውራጃዎችም ሸዋ፣ በጌምድር፣ ላስታ፣ ጎጃም፣ አማራ ሳይንት፣ የጁ፣ ሰሜን ናቸው። (ከ.ብ.ተ.፣ ገጽ 14-15)..

ከላዕላይ ግብፅ በሱዳን በኩል በኋላ የመጡት የቤጋ እና የአገው ሕዝብ እየተሰባጠሩ ቢገቡበትና በዚህም ምክንያት ቤገምድር፣ አገው-ምድር ቢባልም በኋላ ደግሞ ከግራኝ አሕመድ ወረራ በኋላ በኦሮሞች ሥሪት የተነሣ ወሎ ወረይሉ ወረሂመኑ እየተባለና ስሙም እየተለዋወጠ ቢጠራ፣ ቀድሞ ከላይ ከሰሜን ትግሬ፣ ከምዕራብ ቤገምድርንና ጎጃምን፣ ከደቡብ ሸዋን ይዞ በመካከል ያለው ሁሉም የአማራ ግዛት ነበር። (ተ.ጸ.መ.፣ ገ.አ.ወ.፣ ገጽ 8)

ከግራኝ መሸነፍና መሞት በኋላ፣ ኦሮሞች ከአፍሪካ ቀንድ



በብዛት ወደላይ ወደባሌና ወደ አሩሲ ከመግፋታቸው በፊት በሸዋ የነበረው አማራ ግዛቱ በነዚህም አገሮች ላይ የተስፋፋ ነበር። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ. ገጽ 8)

በአምሐራ ሳይንት የሰፈረውና በአንድ በጠቅላላ በአማራ ስም የሚጠራው ሕዝብ በጊዜ ብዛት እርሱ ደግሞ ብዙ ቅርንጫፍ እያበጀ የመሬቱን (የይዞታውን) ሰፋት ወርዱንም ቁመቱንም እያስፋፋ ከትግሬውም፣ ከአገውም፣ ከበጂያውም፣ ከፈላሻውም፣ ከኦሮሞውም በየወሰኑ ላይ በጋብቻና በኑሮ እየተወሐደ (እየተካለሰ) ጎጃሜ፣ ቤገምድሬ፣ ሰሜንኛ፣ ሸዌ እየተባለ ተከፋፍሎ ይኖራል። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 9፣ አ.ኪ.ወ.፣ ገጽ 15) ከተጠቀሱት የአማራ ክፍለ ሀገሮች ውጭ አማራ ከሌሎቹ ጎሣዎች ጋር ተደባልቆና ተዋሕዶ ስለሚኖር ባሁኑ ጊዜ በነዚህ ቦታዎች የአማራ ወኪል ለመምረጥ አዳጋች ይሆናል። ይህም ሁናቴ አማራውን ብቻ የሚመለከት አይደለም። ለምሳሌ ሐረርጌን፣ ሸዋን፣ ወሎን ብንወስድ፣ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የተውጣጣ ዘር በሰላም የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ነው። ስለዚህ፣ በጎሣ ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ማየት አያዳግትም።

የአማራ መንግሥት የመጀመሪያው ነጋሢ የሆኑት ዐፄ ይኩኖ አምላክ (በ1255-1268 ዓ.ም. - ተ.ጸ.መ.፣ ገ.አ.ወ.፣ ገጽ 2) የተወለዱትና እየተማሩ ያደጉት በአማራ ግዛት በሚገኘው በታላቁ ሐይቅ በደብረ እስጢፋኖስ ገዳም ነበር። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 3ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 2)

የዐፄ ይኩኖ አምላክ ተከታዮች እነ ዓምደ ጽዮን (ከ1297-1327 ዓ.ም. - ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ. 3ኛው መጽሐፍ፣ 43-44) እነ ዘርአ ያዕቆብ (ከ1426-1460 ዓ.ም.) መቀመጫቸውን በሸዋ ያደረጉበት ምክንያት በነገድ አንድነት የተነሣ ነበር።

ነገሥታቱ ምንም እንኳን በሸዋ መንዝ፣ ተጉለት፣ የረር ቢቀመጡም በዘመናቸው ሁል ጊዜ የአማሮች የመጀመሪያ መደበኛ ሥፍራ ወደነበረው ወደ ቤተ አምሐራ እየሔዱ በዚያ በየስማቸው ቤተክርስቲያን መሥራት ያዘወትሩ ነበር። በዚህም ምክንያት፣ ደብረ እግዚአብሔርን ሠይፈ አርዕድ፣ መካነ ማርያምን ዘርዓ ያዕቆብ፣ አትሮንስ ማርያምን በዕደ ማርያም፣ መካነ ሥላሴን በፊት ናዖድ የጀመሩትን ልብነ ድንግል አስጨርሰዋል።

## ስለ ነገሥታቱ አመጣጥና ዘር

ምንም እንኳን ባገራችን እጅግ የታወቀው ታሪክ ነገሥት የአክሱም ነገሥታት ከሰሎሞንና ከሳባ ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ የተወለዱና በሙሴ ሕግ መሠረት እውነተኛውን አምላክ የሚያመልኩ እንደሆኑ ቢናገርም፣ በአክሱም ሐውልቶች ላይ የተገኙት የሳባና የግዕዝ ጽሑፎች የአክሱምን ነገሥታት ከቅርብ ምሥራቅ የመጡ፣ በሳባና በግዕዝ የሚጽፉ፣ የጨረቃን አምላክ የሚያመልኩ ስለሚያደርጋቸው የታሪክ ነገሥቱን አባባል ያስተባብለዋል። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 11፣ ከ.ብ.ተ.፣ ገጽ 14-15)

በቋንቋም ረገድ፣ በሳባና በግዕዝ ላይ በዘመኑ የሠለጠነው ዓለም ይጠቀምበት የነበረውን የግሪክ ቋንቋ ሲጨምሩ የዕብራይስጥ ቋንቋ አይታይም ነበር። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ብለን ስንመራመር አጥጋቢ መልስ ለማግኘት አልተቻለም። ስለዚህ፣ ምንም እንኳን በአክሱም ሀውልቶች ላይ የእብራይስጥ ጽሑፍ ባይገኝ፣ ይህን የመሰለ ታሪክ ያለ አንዳች ምክንያትና መሠረት ለብዙ ዓመታት ታምኖበት ሊኖር ስለማይችል የታሪክ ነገሥቱን ታሪክ እንዳልነበረ ለማድረግ በጣም አዳጋች ነው። ምናልባት ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ዐፄ ድል ነዓድ ድረስ ሁለት ሺህ ዓመታት ስላለፉ፣ በነዚሁ ረጂም ዘመናት መካከል የሥልጣን መነጣጠቅና የሥርወ መንግሥት (Dynasty) መለዋወጥ ይሆናል። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 11-12) በሌላ አነጋገር፣ በመጀመሪያ የቀዳማዊ ምኒልክ ዘሮች ከነገሡ በኋላ ሳባውያን ለተወሰኑ ዓመታት፣ ከዚያም እንደገና የቀዳማዊ ምኒልክ ዘሮች ተተክተው ይሆናል።

በዚህ ሁኔታ በመፈራረቅ ሰሎሞናውያንና ሳባውያን ነገሥታት ከቆዩ በኋላ የእስራኤል ተወላጅነት ያላቸው መንግሥትን ወስደው እየመሩ እስከ ዐፄ ድል ነዓድ (ከ850-920 ዓ.ም.) ከደረሱ በኋላ ከሳቸው ላይ ዛጔዎች (ከ920-1255 ድረስ) ወሰዱ። ዐፄ ድል ነዓድ በአክሱም መንግሥት በመጨረሻው በ7ኛው ወይም በ8ኛው መቶ ዓ.ም. ላይ ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት እስራኤላውያን ነገሥታት ተወላጅ ናቸው።

ዐፄ ይኩኖ አምላክ የዐፄ ድል ነዓድ አሥረኛ ትውልድ ስለሆኑ እስራኤላዊ ናቸው ማለት ነው።

ነገሥታቱ ከሰሎሞን ዘር በመውረዳቸው ወይም ወርደናል



ብለው በማመናቸው፣ ለትግሬዎችና ለአማሮች የነገድ አባት ከሆነው ጋር ምንም እንኳን በሴማዊነት በነገደ ዮቅጣንነት ቢዋሐዱም የገዢዎቹ ነገሥታትና የተገዢዎቹ ነገድ የተለያየ መሆኑ ይታያል። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 15-16)

ከቅርብ ምሥራቅ ወደ ኢትዮጵያ የተሻገረው የሳባ፣ የሀበሳን፣ የሂሚያሪት ሕዝብ ዘሩ ከአይሁድም ከሌላውም የሴም ዘር ተደባልቆ በትክክል የይሁዲ ወይም እሥራኤላዊ ዘር ያለውንና የሌለውን አጣርቶ መለየት ፈጽሞ ስለማይቻል፣ ዛሬ ሁሉም በብዛት አብሮ በኢትዮጵያ ሲኖር አማራነቱ ትግሬነቱ ይለይ እንደሆነ ነው እንጂ የዘሩ ልዩነት በጊዜ ርዝመት ጠፍቷል። ስለዚህ ነገሥታቱ ከሰሎሞን ዘራቸውን ቢጠቅሱም፣ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የሚኖሩት የአክሱሞቹ በትግሬነት፣ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ ወዲህ ያሉት ነጋሢዎች ደግሞ በአማራነት ነው። (ተ.ጸ.መ.፣ ግ.አ.ወ.፣ ገጽ 16)

ይህ ሁሉ ስለጥንት ታሪክ የተጠቀሰው የቀድሞውን ለማስታወስ ያህል ነው እንጂ፣ ኢትዮጵያ ባለፉት ሦስት ሺ ዓመታት ውስጥ የተለየ የራሷ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ ያላት ነፃ አገር ስለሆነች፣ ከማንም ጋር ለማዛመድ የታቀደ አለመሆኑ መታወቅ አለበት።

# ክፍል ሦስት

## የአማራው ሕዝብ እና የኢትዮጵያ አንድነት

### ሀ) የግራኝ አሕመድ ወረራ ምክንያት

ኢትዮጵያን የመምራት ሐላፊነት ከአክሱም ወደ ላስታ ከዚያም ወደ ሸዋ በአሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተዛወረ በኋላ፣ ኢትዮጵያን ካጋጠሙአት ችግሮች ዋናውና ተወዳዳሪ የሌለው የግራኝ አሕመድ ወረራ ነበር። ወረራው በአገር ውስጥ የተፈጠረ ቢሆንም፣ ከኢትዮጵያ ውጭ በነበሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች (አረቦችና ቱርኮች) በመሣሪያ ብቻ ሳይሆን በወታደርም እርዳታ የተደገፈ ስለነበረ የኢትዮጵያን መንግሥታዊ ሥርዓትና ሃይማኖት ከመሠረቱ ለማቃወስ ችሏል። ወረራውንም ለመቋቋም ብዙ የጦር መሪዎችና ሠራዊት በጀግንነት ተሠውተዋል።

በቅድሚያ ወረራው የተነሣበትን ምክንያትና የወረራው መሪ ግራኝ አሕመድ ማን እንደነበረ እንመለከታለን። ከዚያም ወረራውን ለመቋቋም የተደረገውን መሥዋዕትነት፣ የደረሰውን ጉዳት፣ የፖርቱጋሎች እርዳታና ድል እንዴት እንደተገኘ ከጠቆምን በኋላ የመሪዎቹንና የወታደሩን ቆራጥነት የአማራውንም አስተዋጽኦ እንገልጻለን።

ለግራኝ አሕመድ መነሣት ዓይነተኛ ምክንያት የሆነው የሃይማኖትና የፖለቲካ ጉዳይ ነበር። በፖለቲካ ረገድ በዚያን ጊዜ የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት በደቡብ ምሥራቅ የነበሩትን የአዳልና የኢሳ ሕዝቦች ያስተዳድሩ ነበር። በሰላም አንተዳደርም ሲሉ በኃይል ያስተዳድሩና ግብር ያስከፍሉ ነበር። ግብር መክፈል የተገዢ ግዴታና የገዢውን ሥልጣንና የበላይነት ማወቅ ሲሆን «አልገብርም» ማለት ደግሞ የገዢውን ሥልጣን መቃወም ነበር። ስለዚህ ነገሥታት በሰላም «አንገብርም» በሚሉ ዜጎቻቸው ላይ በኃይል መጠቀማቸው የተለመደ ነገር ነበር። በኃይል የሚፈጸመውን የማስገበር ተግባርና ቅጣት ዕድል ሲያጋጥማቸው ማለት ኃይል ሲያገኙ ወይም ከእነሱ ጋር የሚተባበር ሲያገኙ ገባሮቹ ሲቃወሙ ቆይተዋል። ይህም ተቃውሞ ግብር ላለመክፈል ብቻ ሳይሆን ገባሪዎቹ እስላሞች አስገባሪዎቹ ደግሞ ክርስቲያን ነገሥታት ቢሆኑም ጉዳዩ ከሃይማኖት አልፎ ወደሥልጣን ሽሚያ አዘንብሎ ነበር።



የደቡብ ዓረቢያ ዓረቦች ከኢትዮጵያ እስላሞች ጋር የንግድና የጋብቻም ግንኙነት መመሥረት ስለጀመሩ፣ የኢትዮጵያ እስላሞች በክርስቲያኑ መንግሥት ተጨቁነናል ሲሉ ዓረቦቹ የመሣሪያና የወታደር እርዳታ ይለግሡ ነበር። ይህም በክርስቲያኖችና በእስላሞች መካከል የነበረውን ሁኔታ በጣም አሻከረው፣ ብዙ ጊዜም ለግጭት ምክንያት ሆነ። በተለይ የእስላሞች ሁሉ የበላይ ጠባቂ የነበረው የቱርክ መንግሥት በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል የተጀመረው ወዳጅነት ስላስቆጣው የኢትዮጵያ እስላሞች መሪና አስተባባሪ የሆነውን ግራኝ አሕመድን ለመርዳት ቆርጦ ተነሣ።

ኢትዮጵያም ነፃነቷንና ግዛቷን ለመከላከል በጊዜው ኃይለኛ ከነበረውና የቱርክ ጠላት ከሆነው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር የመሣሪያና የወታደር እርዳታ ለማግኘት አስፈላጊውን ስምምነት አደረገች። ሆኖም፣ በቦታ ርቀትና በመገናኛዎች ችግር ምክንያት እርዳታው በጊዜው አልደረሰም። ግራኝ አሕመድም በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጥፋት አደረሰ።

### የግራኝ አሕመድ ማንነት

የግራኝ አሕመድ አባት ገራድ ኢብራሂም ይባላል፣ የሕይወት ታሪኩም በትክክል አይታወቅም። የራሱ ስም አሕመድ ቤን ኢብራሂም ኤል ቃዚ ነው። ካደገና የመሪነት ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ ይማም የሚባል የማዕረግ ስም ተጨምሮለታል። ግራኝ የተባለበትም ምክንያት በተፈጥሮው ግራኝ ስለነበረ ነው። እስከዛሬ ድረስ የግራኝ አሕመድ (በልማድ ግራኝ መሐመድ የሚባለው አጠራር ሥህተት ነው) ዘር ከየት እንደሆነ በእርግጥ አይታወቅም። ሐባት (አዳል ውስጥ) ወይም ዘይላ (ሱማሌ) የሚሉ አሉ። የግራኝ እናት የሱማሌዎች ባላባት የማታን ሚስት በመሆኗ ግራኝ ዘሩ ጨርሶ ሱማሌ እንኳን ባይሆን የሱማሌ ዘር ያለው ይመስላል። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ. 4ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 132)

ግራኝ አሕመድ የወጣትነት ጊዜውን ያሳለፈው የአዳልና የዙሪያው ገዢ በነበረው በገራድ አቡን ዘንድ ነበር። ግራኝ አሕመድ የወረራውን ተግባር ሲጀምር በጣም ወጣት (19 ዓመት አካባቢ) ነበር።

ግራኝ አሕመድ በዕድሜ ወጣት ቢሆንም፣ ቆራጥ፣ ዘዴኛና የውጊያ ስልት አዋቂ መሪ መሆኑን ወረራውን ባከናወነባቸው 15 ዓመታት በሥራ አስመስክሯል።

እንሣሡም ያሰፈውን ሁሉ በቀል ለመመለስ፣ ኢትዮጵያንም ለመግዛት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ክርስቲያንነት አጥፍቶ በእስልምና ለመተካት ነበር። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ. 4ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 134)

ይህንንም ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ግራኝ አሕመድ የሚከተሉትን ይፈጽም ነበር፤ ሀ) ከጦር አለቆቹ ምክርና መላ እየጠየቀ መልካሙን ወገን መምረጥ፣ ለ) የጠላቱን ጦር አጥብቆ እያሰለለ እንደሁናቴው የጦር ስልቱን ማስተካከልና ጦርነት መግጠም፣ ሐ) ለፈረሰኛና ለእግረኛ ተዋጊ ጦር የሚመቸውን ሥፍራና ጦር ለይቶ ማወቅ፣ መ) የጦር አለቆች እርስ በርሳቸው እንዳይጣሉ ስለ ምርኮ ሀብት አደላደልና ይዞታ ሕግ ማውጣት፣ ረ) ለዓላማው (ለወረራው ዓላማ) ጠቃሚ መስለው ለሚታዩት ምርኮኞች ምሕረት፣ ለአስጊዎቹ ደግሞ የሞት ቅጣት መስጠት።

በነዚህና በሌሎችም ልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም ግራኝ አሕመድ ብዙ ድሎችን ሊቀዳጅ ችሏል። ወረራው የተጀመረው በ1519 ዓ.ም. ሲሆን ያለቀው ከ15 ዓመት በኋላ በ1534 ዓ.ም. ነበር።

## ከግራኝ አሕመድ ጋር የተደረገው ትግልና የተገኘው ድል

ግራኝን ለአሥራ አምስት ዓመት በጀግንነት የተቋቋሙት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ልብነ ድንግል (ስመ መንግሥታቸው ወናግ (አንበሳ) ሰገድ) ነበሩ። የነገሡት ለ33 ዓመት ነው።

ዐፄ ልብነ ድንግል እንደ ግራኝ አሕመድ አዳዲስ የጦር መሣሪያ ባይኖራቸውም በቆራጥነትና በጀግንነት ተቋቁመዋል።

ሌላ የጎዳቸው ነገር ቢኖር በሰላ ሥራ አለመጠቀማቸው፣ የጠላትን እንቅስቃሴና የጦር ስልት አለማወቃቸውና በጊዜው እርምጃ አለመውሰዳቸው ነበር።

በተደረጉት ልዩ ልዩ ውጊያዎች፣ ግራኝ አሕመድ በውስጥም በውጭም መረጃ ሊጠቀምና የጦር ስልቱንም በሱ መሠረት ሊቀይስ፣ በዐፄ ልብነ ድንግል በኩል በዚህ ዘዴ እምብዛም ሲጠቀሙ አልታየም። ይህም እጅግ ጎድቷቸዋል።

ሆኖም በሥርዓተ መንግሥቱና በሃይማኖቱ ሲኮራ የቆየው



ክርስቲያን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንኳን የመሣሪያና ጥይት እጥረት ቢገጥመውም በጦርና በጎራዴ ጭምር በመጠቀም ተከላክሏል። የፖርቱጋሎች የመሣሪያና የወታደር እርዳታ ስለዘገዩ እርዳታው እስኪደርስ ድረስ የኢትዮጵያ ክርስቲያኑ ሕዝብ ተቃዋሚዎቹን ተቋቋመ፣ ብዙዎችም በጀግንነት ሕይወታቸውን ለአገራቸው አንድነትና ነፃነት ለንጉሠ ነገሥታቸውም ክብር ሠዉ። አንዳንዶቹም ወደ ተቃዋሚዎቻቸው ገቡ፣ ሃይማኖታቸውንም ለወጡ፣ ከዚያም አልፎ በሰላይነትና በመረጃ አቅራቢነት የእስላሙ ወገን አገልጋይና መሣሪያ ሆኑ በወገኖቻቸውም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ። (የሁሉም ዝርዝር ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 4ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 62-71 ላይ ይገኛል)።

ከሸዋ፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከትግሬ፣ ከሐማሴን፣ ከደዋሮ፣ ከባሌ፣ ከይፋትና ከሌሎችም አውራጃዎች የተውጣጣው የዐፄ ልብነ ድንግል ጦር በመሣሪያ ጥራት ቢበለጥም ተስፋ ሳይቆርጥ ጠላትን እየገጠመ የመለሰበት፣ አለቆቹን የገደለበት ወይም ማርኮ ለንጉሡ ያበረከተበት ጊዜ ነበረ። ነገር ግን በግራኝ ጥብቅ ተዋጊነትና በመሣሪያውም ጥራት ምክንያት ጠቅላላው ድል አብዛኛውን ጊዜ የእስላሞቹ ነበር።

ዐፄ ልብነ ድንግል ከብዙ መንከራተት በኋላ ታመው በ45 ዓመት ዕድሜ በ1533 ዓ.ም. ስለሞቱ የግራኝን መሞት አላዩም። ይህ ዕድል የደረሰው ለልጃቸው ለዐፄ ገላውዴዎስ ነበር። (ስመ መንግሥታቸው አጽናፍ ሰገድ፣ በኅዳር በ1533 ዓ.ም. ነገሡ) የሚያሳዝነው፣ ዐፄ ገላውዴዎስ ራሳቸው በጀግንነት ከግራኝ አሕመድ አጎት ከኑር መሐመድ ጋር ሲዋጉ ሞቱ። ሆኖም ኢትዮጵያን 15 ዓመታት ሲወጋ የቆየውን የግራኝ ፍጻሜ ዓይተው ስለሆነ፣ የመንፈስ ደስታ እንዳገኙ አይጠረጠርም።

የፖርቱጋሎች ጀግንነትና የመሣሪያ ጥራት ከክርስቲያኖቹ ኢትዮጵያውያን ቆራጥነት ጋር ለጦርነቱ ወሳኝ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው።

በግራኝ ወረራ ጊዜ የአማራው ሕዝብ አስተዋጽኦ ምን ነበር?

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም ጊዜ እርስ በርሱ ተከባብሮና ተግባብቶ የሚኖር ሲሆን፣ አንድነቱን፣ ነፃነቱንና ሃይማኖቱን የሚጻረር ጠላት ሲመጣ ደግሞ ዘር ወይም ክፍለ ሀገር ሳይል

በአንድ መሪ ሥር ሆኖ ይከላከላል፣ ያጠቃልም። አንዱ ዘር ወይም ክፍለ ሀገር ከሌላው የበለጠ አገሬን እወዳለሁ አይልም፣ ሁሉም ድርሻውን ለማበርከት በሙሉ የመሥዋዕትነት መንፈስ ይሰለፋል፣ ይዋጋልም። ለኢትዮጵያውያን፣ መኖርም ለአገር መሞትም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጎሣና ዘር ወገን ሳይለይ በእኩልነት የሚቀምሰው ጽዋ ነው!! ይህም በየጊዜው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተረጋግጦ ይገኛል።

እስቲ ለጊዜው የዐፄ ልብነ ድንግል ጦር ከየት ከየት እንደሆነ እንይ፣ ከቤገምድር፣ ከትግሬ፣ ከሐማሴን፣ ከሸዋ፣ ከዳሞት፣ ከደዋር፣ ከባሌ፣ ከይፋት፣ ወዘተ ነበር።

እንግዲህ ጦሩ የተውጣጣው በኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት ከሚያምኑት ግዛቶች ከሆነና የሚመራውም ከዚያው ከግዛቶቹ በሆኑት የጦር አለቆች ከሆነ፣ የአማራው ሕዝብ አስተዋጽኦ ጠቅላላ የብሔራዊ ኃላፊነት ስላለበት የሁሉንም ኃይልና ጥረት ማስተባበርና ድርሻውንም እንደሌሎቹ ሁሉ መፈጸም ነበር።

አማራ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ወዘተ የሚባለውም አነጋገር ታሪክ ለመጥቀስ ካልሆነ በስተቀር፣ በዚያን ጊዜ ታሪካዊ ዘሩን በትምክህት መልክ ማለት ራሱን ከሌላው አስበልጦ ለማሳየት (Ethnocentrism) የሚቆጥር አልነበረም። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አገራችን ውስጥ ባለው አብር የመኖርና እርስ በርስ የመጋባት ሁኔታ ምክንያት በጣም ተደባልቋል ወይም ተዋሕዷል። አማራውም ያንጊዜም እንደዛሬው በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምን ስለሆነ ከማንኛውም ጎሣ ጋር ሲተሳሰር ቆይቷል። በዚህም ምክንያት ለሌሎችም ምሳሌ በመሆን የኢትዮጵያን መዋሐድ (Integration) አፋጥኖታል።

ይህንንም በግራኝ ወረራ ጊዜ ከነበሩት ስመ ጥር የጦር አለቆች ዝርዝር መረዳት ይቻላል። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 61-75)

የግራኝ አሕመድ የ15 ዓመት ወረራና ያደረሰው ጥፋት ብዙ ነገር ያስተምረናል። ዋናው ንቁና ቆራጥ መሪዎች፣ ከጊዜው ጋር በሚሔድ መሣሪያ የደረጀ ጦር አስፈላጊነት ነው። በግራኝ ወረራ ዋዜማ በተለይም ዓፄ ልብነ ድንግል ከይማም ማኅፉዝ ጋር በ1508 ዓ.ም. በሐምሌ ወር በይፋት አቅራቢያ ከተደረገው ወረራ እስከ ግራኝ አሕመድ ወረራ ድረስ 10 ዓመታት አልፈዋል። በዚያን ጊዜ ውስጥ



በመንፈሳዊ ጉዳይ የሚያጠፉትን ጊዜ ቀንሰው ለጦር ዝግጅት ያከማቹትንም ወርቅ ለመሣሪያ መግዣ ቢያውሉት ለግራኝ ወረራ ጊዜ በጣም ይጠቅም ነበር። ሌላው ደካማ ጎን፣ የተቃዋሚውን ወገን ትጥቅና ጠቅላላ እንቅስቃሴ ለመሰለል በቂ ጥረት አለመደረጉ እጅግ ጎድቷል።

ምንም እንኳን የኋላ የኋላ በፖርቱጋሎች እርዳታ ኢትዮጵያ ድል ብትቀዳጅም በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጥፋት ደርሷል። ብዙ ገዳማትና አድባራት ከካህናቱና ከመጻሕፍቱ ጋር የእሳት እራት ሆነዋል። የታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም በግራኝ አሕመድ በ1523 ዓ.ም. ሲቃጠል ብዙ መነኮሳት አብረው በፈቃዳቸው ተቃጥለዋል።

የግራኝ አሕመድ ምኞት በሙሉ ኢትዮጵያ የሚገኙትን የክርስቲያን ሹማምንትና መኳንንት ከነንጉሡ ፈጅቶ ገዳማቱንና አብያተ ክርስቲያናቱን አቃጥሎ እርሱ የንጉሡን ሥፍራ፣ የሱ ሹማምንት ደግሞ የንጉሡን ሹማምንቶች ሥፍራ ወስደው ኢትዮጵያን የእስላም አገር፣ የቱርክ መንግሥት ጥገኛ ወይም ተከታይ ለማድረግ ነበር። ለዚህም ምኞቱ ንጉሡን እንደምንም ብሎ ከገደለ ወይም ከማረከ በኋላ አገሩ ሁሉ ለጥ ሰጥ ብሎ ይገዛልኛል የሚል ስለነበረ፣ ጧትና ማታ ንጉሡ ያሉበትንና የደረሱበትን ቦታ ሁሉ እያሰለለና እየተከታተለ ይዋጋ ነበር። ሆኖም አልተሳካለትም!!

ሰሎሞን 'ለሁሉም ጊዜ አለው' እንደሚለው፣ ድል ለማድረግም፣ ድል ለመሆንም፣ ለማጥቃትም፣ ለመጠቃትም፣ ለመዝረፍም፣ ለመዘረፍም ጊዜ አለውና እስከዚህ ጊዜ ድረስ ተጠቂ፣ ተዘራፊ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግራኝ አሕመድን ገድሎ ክብሩን ኩራቱን ነፃነቱንና ሃይማኖቱን በከፍተኛ የ15 ዓመት መስዋዕትነት ለመቀዳጀት በቃ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ጎሣና ዘር ሳይለዩ በአንድ መሪ በመመራት፣ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ በሞታቸው ለኢትዮጵያ ሕያውነትን ሰጥተው አለፉ! ዐፄ ገላውዴዎስም መሣሪያውን እያስረከበ ለሚገባው የግራኝ አሕመድ ጦር የምሕረት አዋጅ አወጁ። ይህም የንጉሠ ነገሥቱን ይቅር ባይነትና ልበ ሰፊነት ያሳያል።

አገራችን ታሪካዊ ጉዞዋን ስትቀጥል ሳለች በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሌላ ለሕልውናዋ አስጊ ሁናቴ አጋጠማት።የግራኝ አሕመድ ወረራ በውጪ እርዳታ ከውስጥ የተሰነዘረ ሲሆን፣ ያሁኑ ደግሞ ከውጪ ጠላት የተሰነዘረ ነበር። እሱም የአድዋ ጦርነት ነው።

### ለ) የአድዋ ጦርነት ምክንያት

ዐፄ ሠርፀ ድንግል (1553-1587 ዓ.ም.) የዐፄ ልብነ ድንግል የልጅ ልጅ ናቸው። ዐፄ ሚናስ በ1556 ዓ.ም. ሲሞቱ ዐፄ ሠርፀ ድንግል ተተከተዋል። ሲነግሡም ዕድሜያቸው አሥራ ምስት ዓመት ነበር። በስመ ጥርነት ኢትዮጵያን 34 ዓመት ገዝተዋል። ለጎንደር መንግሥትና ከተማ እንደመጀመሪያ መሥራችና ቀርጻሪ የሚቆጠሩት እርሳቸው ናቸው።

ስመ ጥር የሆኑበት ዋናው ምክንያት፣ ያለ ዕረፍት በኢትዮጵያ አራቱም አቅጣጫ እየተዘዋወሩ በግራኝ ጦርነት ምክንያት ከኢትዮጵያ ግዛት የተለየውን አገር ስለመለሱና በተለይም ምጽዋን በያዘው በቱርክ ባሻና ከሱ ጋር በተደረበው በባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ላይ ያገኙት ድል አድራጊነት ነው። አቤቶ ዮናኤል የተባለ ደፋር የንጉሡ ዘመድ የቱርኩን ባሻ ጦር ወርውሮ ከወጋው በኋላ ሮጦ በመድረስ በራሱ (በፓሻው) ሠይፍ ራሱን ቆርጦ ለንጉሡ ለዐፄ ሠርፀ ድንግል አምጥቶ የፎከረ ነው። ለሱም «የንጉሡ ሎሌ ዮናኤል ባሻውን ገደለው በሾተል» ተብሎ የድጓ ምልክት ሆኗል። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 232-233) ዓመተ ምሕረቱም 1581 ነበር። ከዚህ በኋላ የምጽዋ ጠረፍ ተመልሶ በንጉሡ በዐፄ ሠርፀ ድንግል እጅ ገባ። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 233)

ቢሆንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ደጃች ውቤ ምስፍንና ድረስ የምጽዋ ጠረፍ ነገሥታቱ ሲበረቱ በነገሥታቱ እጅ፣ የነገሥታቱ ኃይል ሲደክም በቱርኮች እየገባ ቆየ። ምናልባት ያን ጊዜ በዐፄ ሠርፀ ድንግል የሚመራው መንግሥት ደባሩአና ምጽዋ አርኪቆም ላይ ነዋሪ ሠራዊት አስቀምጦ የባሕሩን ዳር ዳር በጥብቅ ቢያስጠብቅ ኖሮ ቱርኮች በዳህላቅ ደሴቶች ብዙ ዘመን በመቀመጥ ጥቅም እያገኙም ነበርና ምጽዋን መልሰው ለመያዝ መቸገራቸው አይቀርም ነበር። ይህም ሲሆን እነሱና ተከታዮቻቸው ግብጾች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ኢጣልያ መግባት  ድረስ መቆየት እንዲሁም ኢጣልያ በእንግሊዝ ረዳትነት ከቱርኮችና ከግብጾች ወስዶ ኢትዮጵያን ለመውጋት አይችልም ነበር። ሆኖም በጊዜው በነበረው የውስጥ ችግርና በስንቅም አቀራረብ ምክንያት ይህ ሊሳካ አልተቻለም። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 232-233)



ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቱርኮች እንደገና ከዳህላቅ ደሴቶች ተነሥተው ምጽዋን ያዙ። ዐፄ ፋሲልም  ማንም ሰው ያለ ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ቱርኮች እንዲቆጣጠሩ አደረጉ። ይህም የሆነው የፖርቱጋልና የእስፓኝ ሚሲዮናውያን ኢትዮጵያን ካቶሊክ ለማድረግ የሚያደርጉትን ሙከራ ለመግታት ነበር። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 267)

ዐፄ ሠርፀ ድንግል ከኢትዮጵያ ላይ የተወሰዱባትን ግዛቶች ለማስመለስ ይዞታዋን ለማስፋፋት የጀመሩትን ተግባር በ19ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት የቀጠሉት ዐፄ ቴዎድሮስ (የካቲት 5/1847 ዓ.ም. የነገሡ)፣ ዐፄ ዮሐንስ (በጥር 13/1864 ዓ.ም. የነገሡ) እና ዐፄ ምኒልክ (ጥቅምት 25/1882 ዓ.ም. የነገሡ) ናቸው።

ዐፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን ለጠላት ከመስጠት የሽጉጣቸውን ጥይት በገዛ እጃቸው ጠጥተው ሲሞቱ ዐፄ ዮሐንስ ደግሞ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ ለኢትዮጵያ ክብር ሕይወታቸውን ሰውተዋል።

ከግራኝ አሕመድ ወረራ ወዲህ በኢትዮጵያ ላይ ፕሮቴክቶሬት በማቆም የአገሪቱን ነፃነትና አንድነት በረቀቀ ዘዴ ለማጥፋት በኢጣልያ መንግሥት የታቀደው ሤራ የአድዋን ጦርነት አስከተለ። ይህንንም ለመቋቋም ሐላፊነቱ የተጣለባቸው ዐፄ ምኒልክ ነበሩ።

ዐፄ ምኒልክ ዐፄ ልብነ ድንግል በግራኝ ወረራ ወቅት ተሸንፈው ከሸዋ ወደ ቤተ አምሐራ ሲሔዱ መንዝ እንዲቆዩ ከተዋቸው ልጃቸው ከአቤቶ ያዕቆብ ትውልድ ሲያያዝ ከመጣው ከሣህለ ሥላሴ  ልጅ ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ይወለዳሉ። ከአቤቶ ያዕቆብ ቢቆጠር ዐፄ ምኒልክ 13ኛ ዘር ናቸው። እናታቸው ወይዘሮ እጅግአየሁ ይባላሉ። ዐፄ ምኒልክ የተወለዱትም በ1836 ዓ.ም. ነሐሴ 12 ቀን ነው።

ለአድዋ ጦርነት (የካቲት 23/1888 ዓ.ም.) ዋና ምክንያት የሆነው ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን የትኛ ግዛት አድርጎ ለመግዛት የነበራቸው ምኞት ሲሆን፣ መንሥኤው ደግሞ በሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም. የተፈረመው የውጫሌ ስምምነት ትርጉም ጉዳይ  ነበር። የስምምነቱ አርእስት የወዳጅነትና የንግድ ቢሆንም  በኢጣልያኖች በኩል የታቀደው ዓይነተኛ ዓላማ በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነት (Protectorate) ለመመሥረት ነበር።

በሁለቱ መንግሥታት መካከል አለመግባባት የተፈጠረው በስምምነቱ 17ኛ አንቀጽ ንባብና ትርጉም ላይ ነበር።የአማርኛው አነጋገር 'የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል' የሚል ሲሆን፣ የኢጣልያንኛው አነጋገር '---ለመላላክ ተስማምተዋል (consent)' ይላል።

በኢትዮጵያ በኩል 'መላላክ ይቻላቸዋል' ለሚለው ሐረግ የተሰጠው ትርጉም 'ከፈለጉ ይችላሉ' ማለት ነው። መፈለግና አለመፈለግ ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መብት ነው። በኢጣልያ መንግሥት በኩል የኢጣልያንኛውን አነጋገር መሠረት በማድረግ፣ ለዚህ አንቀጽ የተሰጠው ትርጉም ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት አማካይነት ለመላላክ ተስማምተዋል የሚል ነበር። ይህም በኢጣልያ መንግሥት አስተሳሰብ መሠረት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነት (Protectorate) ማጽጽሟን ተቀብለዋል ማለት ነው።

የስምምነቱ 19ኛ አንቀጽ 'ይህ አሁን የተደረገው ውል በአማርኛና በኢጣልያ ቋንቋ ትክክል ሆኖ ተገልብጦ ሲያበቃ የታመነ ምስክር ይሆናል' ስለሚል ሁለቱም ወገኖች በየቋንቋቸው በተጻፈው አነጋገር መሠረት ከመከራከር በስተቀር አስታራቂ ሐሳብ አልተገኘም። የኢጣልያኖች ምኞት በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነት ብቻ ሳይሆን ኮሎኒ (የቅኝ ግዛት) ለማጽጽም ስለነበረ፣ የኢትዮጵያን ነፃነት በኃይል መከላከል የግድ አስፈላጊ ሆነ።

ዐፄ ምኒልክ፣ የካቲት 26 ቀን 1877 ዓ.ም. በርሊን ላይ ተሰብስበው ለነበሩት በጊዜው ለታወቁት የአውሮፓ መንግሥታት የኢጣልያ ምኞትና የእርሳቸውን አቋም ካስታወቁ በኋላ ለጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ። የውጫሌውንም ውል በይፋ ሰረዙት (አፈረሱት)።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም. የአምባላጌ ጦርነት ተጀምሮ ከሁለት ሰዓት በኋላ ኢጣልያኖች ሽሽት ጀመሩ። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ ገጽ 88) በተደረገውም ጦርነት ላይ ሜጀር ቶዚሊ በ7 ጥይት ተመትቶ ሞተ። የዐድዋ ጦርነት በየካቲት 23ቀን 1888 ዓ.ም. ተደርጎ ድሉ የኢትዮጵያ ሆነ።



## <u>የዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አስተዋጽኦ</u>

ዐፄ ምኒልክ በጊዜው አገር ውስጥ በነበረው የፀጥታ ሁናቴና በኢጣልያም በኩል ኤርትራን ለመከላከል በተደረገው ዝግጅት ምክንያት፣ እንዲሁም አድዋ በዘመተው ጦር መዳከምና ስንቅ ማለቅ ምክንያት ጦርነቱን ቀጥለው ኢጣልያኖቹን ከኤርትራ ለማስወጣት አልሞከሩም። ዐፄ ምኒልክ ከዐድዋ ድል በኋላ ኢጣልያን ከኤርትራ ለማስወጣት ጦርነቱን ባለመቀጠላቸው በኤርትራውያን ዘንድ ቅሬታ መፍጠሩ የታወቀ ነው። ነገር ግን በተጠቀሱት ምክንያቶች ጦርነቱን መቀጠል ቀላል ውሳኔ አልነበረም። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ. 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 101) ዐፄ ምኒልክ ኤርትራን ለኢጣልያ አሳልፈው እንደሰጡ የሚሰነዘረው ትችት በታሪክ ላይ ያልተመሠረተ ልብ-ወለድ ወሬ ነው። ኤርትራ በኦፊሲዮል የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የሆነችው እ.ኤ.አ. በ1-1-1890 በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት፣ ማለት ከዐድዋ ጦርነት 6 ዓመት በፊት ነበር።

ዐፄ ምኒልክ፣ ኢጣልያንን በዐድዋ ድል በማድረግ የኢትዮጵያን አንድነትና ነፃነት ከማስከበራቸውም በላይ በደቡብና በምዕራብ ከኢትዮጵያ ላይ የተወሰዱባትን አገሮች ሰብስበዋል (Restoration) ለምሳሌ ሐረርጌን ራሳቸው ሔደው በ1879 ዓ.ም. አሚር አብዱላሂን ወግተው አስመለሱ። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 10) ከዚያም ራስ መኰንን የኢትዮጵያን ግዛት ከሐረርጌ ወዲያ ኢሳንና ውጋዴንን አልፎ እስከ ሱማሊያ ወሰን ድረስ አስተዳደሩ። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ 109)

ደጃች ተሰማ ናደው በይሉባቦር በኩል ያለውን አገር የባሮ፡ መሬት እያቋረጡ እስከ ሶባትና ነጭ ዓባይ ድረስ ያለውን አገር አስተዳደሩ (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መጽሐፍ፣ ገጽ109)፣ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ኩሉ ኮንታን፣ ሊሙን ከዚያም እስከ ነጭ ዓባይ ድረስ ፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በቦረና በኩል እስከ ኬንያ ድረስ ያለውን አገር አስተዳደሩ። (ተ.ጸ.መ.፣ ኢ.ታ.፣ 5ኛው መፃሐፍ፣ ገጽ 111)

የቀድሞ መንግሥታት ዳር ድንበር እንደዛሬው በቀዋሚ ምልክቶች የተከለለ ሳይሆን የይዞታቸው ስፋት ወይም ጥበት በኃይላቸው መጠን የተወሰነ ነበር። ኃይለኞች ነገሥታት

ሲነግሡ ወሰናቸው ይሰፋ ነበር። ደካሞች ሲነግሡ ደግሞ የያዙትም ይቀንስ ነበር። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ግዛት እንደመሪዎቿ ሁኔታ ሲሰፋና ሲጠብ ቆይቷል። ሆኖም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሁኔታ በግምት - የተከለለ የድምበር ድንጋይ ባይኖርም - ታውቆ የቆየ ነው። ይህንንም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ይዞታ ለማስከበር በየጊዜው የተነሱት የኢትዮጵያ ነገሥታት ለምሳሌ እነ ዐፄ ልብነ ድንግል፣ ዐፄ ገላውዴዎስ፣ ዐፄ ሠርፀ ድንግል፣ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ዐፄ ዮሐንስ፣ ዐፄ ምኒልክ ከፍተኛ ትግል አድርገዋል። ትግሉም የተካሔደው በደቡብ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሰሜንና በምሥራቅ ኢትዮጵያም ነበር። ለዚህም ዝርዝሩን ከኢትዮጵያ ታሪክ መማር ይቻላል።

ባሁኑ ጊዜ አንዳንድ የኢትዮጵያ አንድነት ጠላቶች አማራ የኦሮሞችን መሬት እንደወሰደባቸውና እነሱንም ተገዢ እንዳደረጋቸው የሚያወሩትና ሌላውንም ለማሳመን የሚያደርጉት ሙከራና ጥረት በታሪክ ላይ ያልተመሠረተ ነው። ምንም እንኳን አንዳንድ የኦሮሞ ጎሣዎች ከ16ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ቢገመትም አብዛኞቹ የመጡት በ16ኛው ዓመተ ምሕረት ነው። (ይልማ ድሬሳ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ገጽ 212-217) በኋላ የመጡ እንደመሆናቸውም መጠን የሰፈሩት፣ እየተስፋፉም የሔዱት አስቀድሞ በተያዘና በቆና ይዞታ ላይ ስለሆነ የተሰነዘረው ሐሳብ ታሪካዊ መሠረት የለውም። አገር ለማስተዳደርና ፀጥታ ለማስከበር በተሠማሩት የመንግሥት ሠራተኞች ላይ የሚሰነዘረው ቅሬታ የሚያንፀባርቀው የጊዜያዊው መንግሥት በሚያበረታታው ጠባብ ብሔረተኝነት ጉጂ ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ከጥላቻ አልፎ እርስ በእርስ መጋደልን እያስከተለ ነው።

አውሮጳውያን አፍሪካን እንደ ቅርጫ በሚከፋፈሉበት ወቅት ዐፄ ምኒልክ በልዩ ልዩ ጊዜና ምክንያት የተበታተኑትን የኢትዮጵያ ግዛቶች ባያስመልሱና ያገሪቱን አንድነትና ነፃነት ባያስከብሩ ኖሮ የኦሮሞዎችና የሌሎችም ዕድል የአውሮጳ ኃያላን የቅኝ ግዥ መሆን ነበር። (Donald N.Levine Wax & Gold p.4)

ስለዚህ የችግራችንን ዓይነተኛ ምክንያት በጥንቃቄ መርምረን በማወቅና በስሜት ብቻ ሳንመራ፣ ሕግና ፍትሕ፣ እኩልነትና ወንድማማችነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ለመገንባት ኃይላችንና ዕውቀታችንን ከበጎ ፈቃድ ጋር አዋሕደን



ለአንዲት ነፃ እናት ኢትዮጵያ መሥራት ይገባል። አንድነት ኃይል፣ መከፋፈል ውድቀትና ድካም መሆኑንም መገንዘብ አለብን።

### ሐ) <u>የ1928 ዓ.ም. መጨረሻው የኢጣልያ ወረራ</u>

ኢጣልያ በአፍሪካ ገጸ ምድር በተለይም በኢትዮጵያ ላይ የቅኝ ግዛት እንዲኖራት ብዙ ጊዜ ይመኙ የነበሩት የኢጣልያ መሪዎች ከኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር ከ18ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ጀምሮ በየጊዜው ተዋግተው ከኮዓቲት በስተቀር የመጨረሻው ድል ሁል ጊዜ ለኢትዮጵያውያን እንደነበረ ሰሓጢና ደጓዓሊ፣ ዐድዋና መቀሌ ከአምባላጌ ጋር ባንድ ቃል ይመሰክራሉ። ምንም እንኳን የጦር መሪዎቹ እነ ዐፄ ምኒልክ፣ እነ ራስ መኰንን፣ እነ ራስ አሉላና ሌሎችም፣ በጠላትም በኩል እነ ጄኔራል ባራቲዬሪና ማጆር ቶማሰ ዲክሪስቶፎርስ ዛሬ በመካከላችን ተገኝተው ሊመሰክሩ ባይችሉም፣ ጦርነቶቹ የተከናወኑባቸው በታዎች የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት እስከ ፍጻሜ ዓለም ድረስ ሲያስታውሱ ይኖራሉ።

በነዚህ ጦርነቶች ውጊያው ይካሔድ የነበረው በመጠኑም ቢሆን በተመሳሳይ የጦር መሣሪያዎች ስለነበረ፣ ማለት አኤሮፕላንና የጋዝ ጢስ መርዝ ስላልነበረ፣ ኢትዮጵያውያን ቆራጥነታቸውንና ጀግንነታቸውን አስመስክረዋል።

የኢጣልያ መንግሥት የዐድዋውን ውርደት ለማደስና ቂም በቀሉን ለመወጣት፣ ለ40 ዓመታት ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎችና የመርዝ ኬሚካሎች ሲያዘጋጅ ከቆየ በኋላ የሠለጠነውን ዓለም ሕግና 1920 ዓ.ም. ከኢትዮጵያም ጋር የተፈራረመውን የወዳጅነት ውል በማፍረስ እሥራ ላይ ሊያውላቸው ወሰነ፣ አዋላቸውም።

ምንም እንኳን ይህ አፈጻጸም የኢትዮጵያውያንን የመዋጋት መንፈስ ባይቀንሰውም ለመቋቋም አልተቻላቸውም። በሰሜን፣ በማይጨው፣ በደቡብና በሌሎችም የጦር ግንባሮች የተሰለፉት የኢትዮጵያ ጀግኖች በቦምብና በጋዝ መርዝ ጢስ አለቁ!!

በየጦሩ ግንባር ለአገራቸው ነፃነት ለመሰዋት ከተሰለፉት የጦር መሪዎች ውስጥ የጥቂቶቹን ስም እንጠቅሳለን፣ እዚህ ያልተጠቀሱትን መሪዎችና ጀግኖች ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

## በሰሜን የጦር ግንባር

ራስ እምሩ፣ ራስ ካሣ፣ ራስ ሥዩም፣ በጅሮንድ ለተ ይበሉ፣ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ፣ ደጃዝማች በየነ ሀብተ ማርያም፣ ቢትወደድ መኮንን ደምሰው፣ ራስ ሙሉጌታ፣ ደጃዝማች መንገሻ ይልማ፣ ሌሎችም።

## በደቡብ የጦር ግንባር

ደጃዝማች በየነ መርዕድ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ገ/ማርያም፣ ቀኛዝማች መኩሪያ ተሰማ፣ ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል፣ ደጃዝማች (በኋላ ራስ ቢትወደድ) መኩንን እንዳልካቸው፣ ደጃዝማች ዐምደ ሚካኤል ነበሩ። ምንም እንኳን በጋዝ መርዝ ጢስና በአኤሮፕላን በምብ ውርጅብኝ ምክንያት የኢትዮጵያ ጀግኖች የጠላትን ጦር ለመመከትና ለማቆም ባይችሉም፣ በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል።

በአምስቱም የጠላት ወረራ ዘመን ኢትዮጵያውያን አርበኞች በዱር በገደል ተሰደው በጠላት ላይ አደጋ እየጣሉ መውጫ መግቢያ በማሳጣት ሲያባንኑት ኖረዋል።

የአገሪቱም መሪ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጠላትን ሕገ ወጥ ጦርነትና በጋዝ መርዝ ጢስ መጠቀም ለዓለም መንግሥታት ማኅበር (League of Nations) ጄኔቭ ላይ በመገኘት አስታውቀው ነበር። ሆኖም የተደረገው የዲፕሎማቲክ ትግል ኢትዮጵያን ከሙሶሊኒ መንጋጋ ውስጥ ሊያወጣት አልቻለም። በ1933 ዓ.ም. ነፃነቷን እንደገና እስከተቀዳጀችበት ወቅት ድረስ ኢትዮጵያ በጠላት ይዞታ ስር አትወድቅም በማለት ምቹ ሥፍራዎችን እየመረጠ አርበኛው ለአምስት ዓመታት ተዋግቷል።

ኢትዮጵያ እንደ አንድ ነፃ አገር መኖር ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ፣ ሕልውናዋን ለማጥፋት ከውስጥም ከውጪም በየጊዜው መሞከሩ አልቀረም። ሆኖም በዘመናት መካከል ያጋጠሟትን ፈተናዎች ሁሉ በጀግኖች ልጆቿ መሥዋዕትነት እየተቋቋመች እስከዛሬ ቆይታለች።

## የአማራው ሕዝብና የኢትዮጵያ አስተዳደር

በነዚህ ረጂም የታሪክ ዘመናት ውስጥ አማራው ሕዝብ የተጣለበትን ሐላፊነት በማክበር፣ በታላቅ ቁራጥነትና ግምባር



ቀደምትነት፣ ከሌሎቹ አማራ ካልሆኑት ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበርና በማስተባበር ድርሻውን አበርክቷል።

ኢትዮጵያን የመምራት ሐላፊነት በአሥራ ሁለተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ከአክሱም ወደ ዛጔ ከዚያም በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመን ወደ አማራው ሕዝብ ከተዛወረ በኋላ ኢትዮጵያን ባጋጠሟት ታላላቅ ወረራዎች፣ ማለት በውጪ ጠላቶች በተደገፈውና ከውስጥ በተነሳው የግራኝ አሕመድ ወረራና እንዲሁም ከኢጣልያ ሁለት ጊዜ በተሰነዘሩት ወረራዎች ወቅት የኢትዮጵያ መሪዎች ያሳዩትን የመሪነት ችሎታና የወታደርቹንም ቁራጥነትና ጀግንነት በመጠኑም ቢሆን ተመልክተናል።

እነዚህ ሦስት ወረራዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ስለያዙ ተጠቀሱ እንጂ አማራው ሕዝብና መሪዎቹ ተመሳሳይ አቋም ከያዙ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር ባለፉት 700 ዓመታት ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት በየጊዜው ያቀረቡት መሥዋዕትነት ብዙ ነው። ይህም መሥዋዕትነት፣ እንደማንኛውም አገር አፍቃሪ ኢትዮጵያዊ የተደረገ ነው እንጂ፣ የአማራው ሕዝብ ትሩፋት ብቻ አለመሆኑ መታወቅ አለበት። በአንዲት ነፃ አገር ኮርቶ መኖርና ያገርም ነፃነት ሲደፈር መከላከልና መሥዋዕት መሆን የኢትዮጵያውያን አንድነት ሰንሰለት ነው። ይህንንም የኢትዮጵያ ታሪክ በማያወላውል አኳኋን ይመሰክራል። ኢትዮጵያ ያንድ ጎሳ ወይም ነገድ ብቻ እናት ስላልሆነች እና ሁሉንም በእኩልነት ደረጃ ስለምትመለከት፣ ክብሯን ለመድፈር ጠላት በተነሣ ጊዜ ልጆቿ በጐሣዊነት ስሜት ሳይለያዩ በኅብረትና በቁራጥነት መንፈስ መሥዋዕት ሆነውላታል።

ነገር ግን ሃይማኖትን ከአገር ጉዳይ፣ የአስተዳደርን ሐላፊነት ከጎሣ ታማኝነት ለመለየት ያቃታቸው ክፍሎች በውጪ አነሳሾች በመገፋት፣ ባገርና በወገን ላይ በየጊዜው ጉዳት ማድረሳቸው የታወቀ ነው። በዚያው አንጻር የአገራቸውንና የወገናቸውን ዘላቂ ጥቅም ወደጎን በማድረግና በጊዜያዊ ነገር በመሸንገል ለጠላት በመሰለልና መሣሪያም በመሆን አገራቸውን የጎዱ አልጠፉም። ይህም የሰውን ልጅ ደካማ ጎን በይፋ ያሳያል። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ይሁዳም ስለነበረ እምብዛም አያስደንቅም!!

በአስተዳደርም ረገድ፣ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ ጀምሮ ያለውን የኢትዮጵያ መንግሥታዊ መዋቅር ብንመለከት፣

በሲቪልም ሆነ በጦር መስክ የጎላ ልዩነት አናይም። በአመራር ደረጃም እንኳን ሲታይ ባለፉት 117 ዓመታት ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ የነበሩትን የኢትዮጵያ ርዕሰ ብሔሮች ስንመለከት 43.9% ወደ አማራው፤ 41% ወደ ኦሮሞው፤ 15.1% ወደ ትግሬው ጎሣዎች የሚያደላ እንደነበረ የታወቀው የኢትዮጵያ ጥናት ምሑር ክሪስቶፈር ክላፋም ካደረገው ጥናት (Political Economy of Ethiopia edited by Marinal Ottoway p.221-231) ለመገንዘብ ይቻላል። ክላፋም Revolutionary Ethiopia በተባለው መጽሐፍ የኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር - የመንግሥቱ ኀይለ ማርያምን ጨምሮ - የአማራው ብቻ አለመሆኑን፤ ሌሎች ብሔረሰቦች የተሳተፉበት፤ በአጠቃላይ የብሔረሰብ ጉዳይ ወደ ውሕደት ደረጃ የደረሰ መሆኑን ያስገነዝባል። በእርግጥ በመንግሥቱ ኀይለ ማርያም አስተዳደር ውስጥ ከመንግሥት ጋር በነበው ቅራኔ ምክንያት በአጠቃላይ የትግሬው ብሔረሰብ (ኤርትራን ጨምሮ) በከፍተኛ ደረጃ ላይ ተሳትፎው መጠነኛ እንደነበር አይካድም።

ባሁኑ ጊዜ አንዳንድ ጠባብ ብሔረተኞች የኢትዮጵያን ታሪክ ለፖለቲካ እንዲአመቻቸው በመቆራረጥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ አንዳንዱን ብቻ አጥፊና በዳይ ሌላውን ክፍል ተበዳይ በማስመሰል የሚነዙት ልብ ወለድ ወሬና የጥላቻ መርዝ መሠረት የሌለው ለመሆኑ ከላይ የተገለጸው በቂ ማስረጃ ነው።

በረጂሙ የአገራችን ታሪክ ሒደት ውስጥ አንዳንድ የአስተዳደር ጉድለቶች ካሉ፤ ሊኖሩም ይችላሉ፤ በአጥፊዎቹ ግለሰቦች ላይ አስተያየት ከነማስረጃው ሊሰነዘር ይቻላል፤ ይገባልም። ነገር ግን እንዲያው በደፈናው ያለ አንዳች ማስረጃ አስተዳደሩ የጋራ እያሌ ብሔረሰቦች የሚሳተፉበት ሆኖ ሳለ ጥፋትን ለአንዱ ብሔረሰብ ብቻ ማከናነብ ፍርደ ገምድልነት ነው።

በመንግሥት ደረጃም፤ የአስተዳደር ጉድለትን ስለሚመለከት ጉዳይ የሚሰነዘረው ትችት በመሪው ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን፤ በሐላፊነት ቦታ የተቀመጡትን ባለሥልጣኖች ጭምር ስለሚያስጠይቅ፤ ሐላፊነታቸው በድምርም በነጠላም መታየት አለበት።

ምንም እንኳን አገራችን በየጊዜው የተለያዩ ችግሮች ከውስጥም ከውጭም ቢያጋጥሟት፤ ይሁን ሁሉ የታሪክ



ማዕበል በቆራጥ ጀግኖች አባቶቻችን መሥዋዕትነት አሳልፋ ከኛ ዘመን ደርሳለች።

የዛሬው ትውልድ ዓይነተኛ ሐላፊነትና ግዴታ ደግሞ የአገራችንን አንድነትና ነፃነት እንደ ዐይን ብሌን በመጠበቅ፤ እኩልነት፤ ወንድማማችነት፤ እህትማማችነት እና መከባበር፤ በጠቅላላው የሕግ የበላይ ገዢነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ መመሥረትና ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ መሆን አለበት። የብሔረተኛነትና የጎሣዊነት ስሜት መፋጀትን እንጂ ልማትንና ዕድገትን አለማስከተሉንም መረዳት አለብን።

እኛን በቀጥታና በቅርብ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ደግሞ ቤኒቶ ሙሶሊኒ በተፈጥሮና ከሒትለር በተማረው ዘረኝነት ተመርዞ በኢትዮጵያውያንና በራሱ በኢጣልያ ሕዝብ ላይ ያመጣው መዓት ጉልህ ምሳሌ ነው።

# ክፍል አራት

## የአማራው የትምህርት አስተዋጽኦ

ዘመናዊ ትምህርት በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት (እ.ኤ.አ. 1907) ወደ ኢትዮጵያ መግባት እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ፤ ባገራችን ሰፍና የነበረው የባሕል ትምህርት - ቅኔ፤ ጾምትወ ዜማ፤ አቋቋምና ትርጓሜ መጻሕፍት - ነበር። እሱም የሚካሄደው በየአብያተ ክርስቲያናቱና ገዳማቱ ሲሆን አስተማሪዎቹም ካህናቱና ሊቃውንቱ ነበሩ።

ለመጥቀስ የሚፈለገው አማራው ሕዝብ በባሕል ትምህርት ረገድ ያደረገውን አስተዋጽኦ ባጭሩ ስለሆነ፤ ስለ ግዕዝ ፊደል አመጣጥ ታሪክ፤ ስለ ቅኔ፤ ስለ ዜማ፤ ስለ መጻሕፍት ትርጓሜ (አንድምታ) እና ስለ አማርኛ ሥነ ጽሑፍ ዝርዝር መግለጫ አይሰጥም።

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበትና የመጀመሪያውም ጳጳስ አባ ፍሬምናጦስ (Frumentios) በአራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት በእስክንድሪያው ፓትርያርክ በአቡነ አትናቴዎስ ተሹመው ከመጡ በኋላ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሕዝቡን የመስበክና ሕፃናቱን የማስተማር ግዴታ ወስዳ ዘመናዊ

ትምህርት ወዳገራችን እስከገባበት ጊዜ ድረስ ግዴታዋን ስታከናውን ቆይታለች። ዛሬም ቢሆን፣ በተለይ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች በማይገኙባቸው ገጠር ሰፍራዎች እያስተማረች ናት። ትምህርቱም መሠረታዊ ፊደል ቆጥር ማንበብና መጻፍ ብቻ ሳይሆን ቅኔ መቀኘትን፣ ጸዋትወ ዜማንና የመጻሕፍት ትርጓሜንና ምርመራን ይጨምራል።

ግዕዝ ሕያው ሆኖ ለመቆየት የቻለው የቤተክርስቲያን መገልገያ ቋንቋ - ንባብ፣ ቅኔ፣ ዜማ - በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሥነ ጽሑፍም ማኅደር ስለሆነ ነው። የኋላ ኋላ አማርኛም ሊስፋፋና የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ሊሆን የቻለው ቤተክርስቲያን ለምእመናን መስበኪያ፣ ሊቃውንት ለአንድምታ (ትርጓሜ)፣ ቤተ መንግሥት ለአስተዳደርና ለፍርድ ተግባር ከአሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲጠቀሙበት በመቆየታቸው ነው።

ይህን የዕውቀት ችቦ ከአንዱ ትውልድ ወደሌላው እንዲወርድ ያደረጉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ናቸው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፊደል አስቆጣሪዎቹ እስከ መጻሕፍት ትርጓሜ አስተማሪዎቹ ባለውለታ ነው። እነሱ ብራና ፍቀው ቀለም በጥብጠው የሥነ ጽሑፍ ቅርስ ባያቆዩልን ኖሮ ዛሬ የምንኮራበት የሥነ ጽሑፍ ቅርስ አይኖረንም ነበር።

በእርግጥ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣልን የሥነ ጽሑፍ ቅርስ በብዛት መንፈሳዊ ነው። አብዛኛውም ትርጉም ነው። የግሪኮችን፣ የሮማውያንና የሌሎችንም የመሰለ ክላሲክስ የለንም።

ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሎች በተለይ አውሮጳውያን ዕውቀት ሲገበዩና ሲያስፋፉ ኢትዮጵያ በሃይማኖትና በፖለቲካ ምክንያት የሥነ ጽሑፍና የሳይንስ ዕውቀት የመለዋወጥ ዕድል ሳይደርሳት መቅረቱ ነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ለእኛ የደረሱን በትርጉም የሆነበት ምክንያት፣ ብሉይ በእብራይስጥ፣ ሐዲስ ደግሞ በግሪክ ስለነበረ የተጻፉት መላው ዓለም በየቋንቋው ሲተረጉም የኛም ሊቃውንት መጀመሪያ ወደ ግዕዝ በኋላ ደግሞ ወደ አማርኛ ተርጉመውልናል።

በጠቅላላው የስነ ጽሑፍንና ሥነ ፍጥረትን ዕድገት ስለሚመለከተው፣ አገራችን እንደ አንድ ደሴት ለብቻዋ



ሳትወድ በግድ ለሕልውናዋ እየታገለች እንድትኖር በአካባቢው ሁናቴ በመገደዷና ከሰለጠነው ዓለም ጋር ግንኙነት ስላልነበራት እንደነ ግሪክ፣ ሮማውያንና ሌሎችም በሥነ ጽሑፍና ሥነ ጥበብ መራመድ አልቻለችም።

ከዚህም በላይ ዮዲትና ግራኝ አሕመድ በማከታተል ካህናቱንና ሊቃውንቱን ስለጨረሷቸው መጻሕፍቱንም ስላቃጠሏቸው የሥነ ጽሑፍ ቅርስ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ይኖራል ተብሎ አልተገመተም ነበር። ግን እግዚአብሔር አገራችንን ከቶ አልተዋትም!!

ምንም እንኳን የአገራችን የባሕል ትምህርት እንደዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርት የተቀነባበረ ባይሆንም፣ የራሱ ሥነ ሥርዓት አለው። የዘመኑንም ፍላጎት በመጠኑም ቢሆን አርክቷል፣ ለአዲሱም ምዕራባዊ ሥልጣኔና ትምህርት መሸጋገሪያ ድልድይና መሠረት ሆኖአል። በዚህ ጽኑዕ መሠረት ላይ ዘመናዊ ትምህርትና ሥልጣኔን መገንባት የወጣቱ ትውልድ ድርሻ ነው።

መሸጋገሪያ ድልድዩን የሚያፈርስ መመለሻ የሌለው መሆኑ የታወቀ ስለሆነ፣ የራስን ታሪክና ቋንቋ መዘንጋትም ቤትን ያለምሰሶ ለማቆም እንደመሞከር ይቆጠራል። ያገርን ቅርስ ወደኋላ ትቶ ያልሆኑትን ለመሆን መሞከር ከማስገመቱም በላይ ከንቱ ሙከራ ነው!!

የሀገራችን የባሕል ከፍተኛ ትምህርት ዋና ዋና መስኮች የሚከተሉት ናቸው። ቅኔ፣ ጸዋትወ ዜማ (ድጓ፣ ምዕራፍ፣ መሥዋዕት)፣ ቅዳሴ፣ የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ (አንድምታ)፣ የብሉይ ትርጓሜ (አንድምታ)፣ የሐዲስ ትርጓሜ (አንድምታ)፣ የመጽሐፈ ሊቃውንት ትርጓሜ (አንድምታ)፣ እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ባዊርስ፣ ባስልዮስ፣ ካልዕ ጊዮርጊስ፣ አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ፣ ወዘተ፣ መጽሐፈ መነኩሳት (አንድምታ)።

አማራው ሕዝብ በትምህርት በኩል ያደረገው አስተዋጽኦ ጎልቶ የሚታየው በባህል ትምህርት ረገድ ነው። በዘመናዊ ትምህርት፣ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመማርም ሆነ በማስተማር ረገድ አማራው እየተሳተፈ ነው።

አማራው ሕዝብ በባሕል ትምህርት በኩል ያቀረበው አስተዋጽኦ፣ ማለት ብራና ፍቆና ቀለም በጥብጦ ግዕዝን ሕያው የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ አድርጎ ማቆየት፣ አማርኛን

የአማርኛ መነጋገሪያ ቋንቋ ብቻ ከመሆን አልፎ በቅኔና በመጻሕፍት ትርጓሜ አማካይነት የኢትዮጵያውያን ሁሉ መገናኛና የጋራ ቅርስ እንዲሆንና የሥነ ጽሑፍ የቅኔና የዜማ ቅርስ ለትውልድ እንዲደርስ ያደረገው ጥረት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

ኢትዮጵያን ከሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች የተለየች የሚያደርጋት የሥነ ጽሑፍ ቅርሷና በልጆቿ መሥዋዕትነት ነፃነቷን ጠብቃ መኖሯ ነው።

የአክሱም መንግሥት ይፋዊና የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ግዕዝ ቢሆንም ሕዝቡ በኋላ ይነጋገር የነበረው ከግዕዝ በተወለደው በትግርኛ ነበር። የመንግሥት ሥልጣን ከአክሱም ተከዜን ተሻግር በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ወደ ዛጔ ሲዛወር፣ ትግርኛ እዚያው የሕዝብ ቋንቋ ሆኖ ቀረ። ከዛጔዎች ደግሞ ሥልጣን ባሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ አማራው ሲዛወር አማርኛ ከግዕዝ ጋር የመንግሥት ቋንቋ ሆኖ ጥቂት በጥቂት ግዕዙ ለመንፈሳዊ ጉዳይ፣ አማርኛው ለአስተዳደር ማገልገል ጀመረ።

አማርኛ ግዕዝን የመሰለ ጽኑዕ መሠረት ስላለው፣ በጣም እየጠነከረና እየተስፋፋ ሔደ። ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችና ከውጭ አገር ቋንቋዎች ቃላትና ሐረግ በመዋስ ጎለመሰ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የአስተዳደርና የሕግ፣ በተጨማሪም የኢትዮጵያውያን ዋና መገናኛ ቋንቋ ለመሆን በቃ። በዚህም ምክንያት ቀዳሚና ደጎሬ ሳይለይ ለሁሉም የጋራ ቅርስ ነው ለማለት ይቻላል።

አማርኛ የአስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ለብዙ ዘመናት በመቆየቱ፣ ትግርኛ ተናጋሪው ዓፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸው ይጠቀሙ የነበረው በአማርኛ ነበር። ይህም ባማርኛ መሥራት ከጥንት የመጣ መሆኑን ያስረዳል።

ይህን የመሰለ የሚያኮራ የጋራ የሥነ ጽሑፍ ቅርስ ሲኖረን፣ አንዳንድ የኦሮሞ ሕዝብ ተጠሪ ነን ባዮች ከግዕዙ ፊደል ይልቅ የላቲኑ ለኦሮምኛ ድምፅ ይቀርባል በሚል ምክንያት ኦሮምኛውን በላቲን ፊደል ለመጻፍ ሐሳብ መሰንዘራቸው ያስገርማል።

'በከልቻ ኦሮሚያ' በሚል ስያሜ በላቲን ፊደል የሚዘጋጀውን ጋዜጣ መነሻ በማድረግ፣ ከግእዝ ፊደል ይልቅ የላቲን የተመረጠበትን ምክንያት አቶ ሌንጮ ለታ የኦሮሞ



ነፃነት ግንባር ም/ዋና ጸሐፊ ሲያስረዱ 'የሀገር ውስጥና የውጪ የቋንቋ ሊቃውንት ስለዚሁ ተጠይቀው ትክክለኛውን የኦሮምኛ ቋንቋ ለመጠቀም የላቲን ፊደል መምረጣቸውን አስታውቀዋል' ይላሉ። (አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት 8 ቀን፣ 1984 ዓ.ም.)

አቶ ሌንጮ እንደሚሉት የላቲን ፊደል የተመረጠው የቋንቋ ሊቃውንት በሰጡት አስተያየት ከሆነ፣ የተባሉት ሊቃውንት በግዕዝና በላቲን ፊደሎች መካከል ያለውን የድምፅ ልዩነት በሚገባ ስላልተገነዘቡ፣ የአስተያየታቸው ትክክለኛነት ያጠራጥራል።

ለምሳሌ

| የኦሮሞ ቃል | በላቲን ፊደል | በግዕዝ (በአማርኛ) ፊደል |
|---|---|---|
| ዋቃ | Waka | ዋቃ |
| ቆጮ | Kotcho | ቆጮ |
| ጤዴሳ | Tedesa | ጤዴሳ |
| አውጥ | Aut | አውጥ |
| ጡሙጋ | Tumuga | ጡሙጋ |
| ጣፊ | Tafi | ጣፊ |
| ጫልቱ | Chaltu | ጫልቱ |
| ዱጊ | Dugi | ዱጊ |

ለኦሮምኛው አነጋገር ከግዕዙና ከላቲኑ ፊደል የትኛው እንደሚቀርብ ለምሳሌ በቀረቡት ቃላት አስረጂነት አንባቢ መፍረድ ይችላል።

በተጨማሪ አቶ ሌንጮ 'የአማርኛ ፊደል ከሁለት መቶ በላይ በመሆኑ ሕዝብን ለማስተማር የሚወስደው ጊዜ ሰፊ' መሆኑን ገልጠዋል። እዚህ ላይ አቶ ሌንጮ ተሳስተዋል። የኢትዮጵያ ፊደላት 33 ናቸው። የያንዳንዱ ፊደል 6 ዘርፎች ለብቻቸው እንደ ፊደል አይቆጠሩም። አጭር ጊዜ እንደሚፈጅም በደርግ ዘመን በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በማስተማር የተሳተፉ ወጣቶች ሊያትቁበት ይችላሉ።

ይህ ሐሳብ የተሰነዘረው የተሰጠውን ምክንያት ደካማነት ለመጠቆምና ትክክለኛውን ሁናቴ ለማስረዳት ነው እንጂ ኦሮሞች ቋንቋቸውን በሚፈልጉት ፊደል መጻፍ መብታቸው መሆኑ የታወቀ ነው።

ስለሆነም፣ ምናልባት እርምጃው የተወሰደው በሰምና ወርቅ ዘይቤ በአማራ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለመግለጽ ከሆነ፣ የኢትዮጵያ ፊደሉች የተገኙት የኢትዮጵያውያን ሁሉ የጋራ ቅርስ ከሆነው ከግዕዝ እንጂ አማሮች የፈጠሩት አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

እርሞች ያላስታወሱት ነገር ቢኖር የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የነሱም ጭምር እንጂ የአማሮችና የትግሮች ብቻ አለመሆኑን ነው።

## ክፍል አምስት

### የአማራውና አማራ ያልሆኑ ነገዎች ግንኙነት

በተደረገው ጥና መሠረት (Getatchew Haile, Democracy in Post-Derg Ethnic Ethiopia, IMBYLTA, No.3/4 p.5 and World Data, Encyclopaedia Britannica, p.384-385 1991) ኢትዮጵያ ውስጥ ባሁኑ ጊዜ የተለያየ ቋንቋና መጠን ያላቸው ከ70 እስከ 100 የሚደርሱ ነገዎች ወይም ነገዶች ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ በሰው ብዛት ብልጫ ያላቸው እርሞ፣ አማራና ትግርኛ ተናጋሪዎች (ትግራይና ኤርትራ) ናቸው። ከነዚህ ከሦስቱ ክፍሉች ሁለቱ ማለት አማራና ትግርኛ ተናጋሪዎቹ ነባር ሲሆኑ፣ እርሞች ወደ ኢትዮጵያ በብዛት የገቡት በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። (ይልማ ዴሬሳ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ገጽ 212-217) ከአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት አንዳንድ የእርሞ ነገዎች በተለያዩ ጊዜያትና መጠነኛ ቁጥር ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውና በደቡብ በኩል መሥፈራቸው ይነገራል።

የቀሩት ልዩ ልዩ ነገዎች መቼና ከየት እንደመጡ፣ እንዲሁም በረጂሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እርስ በርሳቸው፣ ከሌሎችም ጎረቤቶች ጋር በምን ዓይነት ግንኙነት እንደኖሩ አለቃ ታየ ያስረዳሉ። (ከአለቃ ታየ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ)

ግንኙነታቸውም አንዳንድ ጊዜ ሰላማዊ ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ በግጭትና በጦርነት ላይ የተመሰረተ ነበር።



ጉርብትና ሰላማዊ ሲሆን ጋብቻን፣ ጋብቻ ደግሞ ዝምድናን እና ወዳጅነትን እየመሰረቱ ልዩ ልዩ ነገዎችን ለማቀራረብ ይችላሉ፣ በአንዳንድ አካባቢም ችለዋል።

በተጨማሪ ንግድና ሌሎችም ግንኙነቶች ልዩ ልዩ ነገዎችን ስለሚያቀራርቡ በመካከላቸው የሚኖረው መፈራራትና ጥላቻ ሊጠፋ ይችላል። ይህን የሚያስረዱም በአገራችን ጥሩ ምሳሌዎች አሉ።

በዚህ ምክንያት ዛሬ በአገራችን የሚኖሩት ልዩ ልዩ ነገዎች፣ ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኞቹ በንግድ በጣም ስለተቀራረቡና በጋብቻም ስለተዋሐዱ የነገ ግንዳቸውን ለታሪክ ያህል ከመጥቀስ በስተቀር ጥርት ያለው የእከሌ ነገ ወገኖች ነን ለማለት አይችሉም።

ይህም ሁናቴ በሕዝቡ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በነገሥታቱም ያለ ነበር። ከሕዝቡ ጋር በጋብቻ ተቀላቅለዋል። ይህንንም የኢትዮጵያ ታሪክ በግልጽ ያስረዳል።

ስለዚህ፣ በዛሬው ጊዜ ከአንድ ነገ ወይም ነገድ ብቻ የተገኘና የሌላ ነገ ደም ያልተቀላቀለበት ሰው ለማግኘት እጅግ አስቸጋሪ የሚሆነው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለምም ነው። የሠለጠነው ዓለም ሕዝብ ዛሬ ጊዜ ነገን የሚያነሳው (የሚጠቅሰው) ለታሪክ ያህል ነው እንጂ ሌላ ዋጋ ለመስጠት አይደለም።

ስለዚህ ነገ የፖለቲካ መመሪያ ፍልስፍና መሆን የለበትም። በነገ ላይ የተመሠረተ ፍልስፍና ራስን ከፍ ሌላውን ክፍል ዝቅ አድርጎ የሚመለከት ስለሆነ (Ethnocentrism) በመሠረቱ ጠባብ አስተሳሰብና፣ ብሔረተኝነት ነው። የሶቭየት ኅብረትና ዩጎዝላቪያ ፖለቲካቸውን በነገ ፍልስፍና ላይ በመገንባታቸው የደረሰባቸውን ከፍተኛ ችግር እነሆ እየተመለከትን ነው።

በነገ ላይ የተመሠረተ ፍልስፍና ጠባብ ብሔረተኝነትን ስለሚያዳብር አፍራሽ እንጂ ገንቢ ባሕርይ የለውም። ኢትዮጵያውያን የሶቭየት ኅብረትንና የዩጎዝላቪያን ስሕተት ለመድገም ብንሞክር፣ ዓይን ጨፍና ገደል እንደ መግባት ወይም የወፍጮ ድንጋይ ከወገብ ላይ አንግቦ ለመዋኘት እንደመሞከር ያለ አደገኛ ድርጊት ነው።

በተጨማሪ፣ በነገ ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ እንደ

እምቧይ ካብ በቀላሉ የሚናድና ዘላቂነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ለመጪው ትውልድ ቂምና በቀል ያተርፋል።

ስለዚህ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት የግለሰብ መብትን በሚያከብር የፖለቲካ ፍልስፍና ላይ መገንባት አለበት። የያንዳንዱን ግለሰብ መብት መጠበቅና መከበር ደግሞ ሁሉንም ዜጋ ጎሣና ጾታ ሳይለይ በእኩልነት የሚመለከት ስለሆነና የአስተዳደር ድንበር ስለሌለው የይለፍ ወረቀት አይጠይቅም።

ሊኖረን የሚገባው የአስተዳደር ፍልስፍና ይህን የመሰለ መሆን ሲገባው፤ በጎሣ ላይ የተመሠረተው በኢሕአዴግ አባሎች ቀደም ሲል ተነድፎና ተጠናቆ በአለፈው ሐምሌ ወር አዲስ አበባ በወጣው የሽግግር ወቅት ቻርተር ውስጥ ጉልህ ሆኖ የሚታየው የፖለቲካ መመሪያ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚከፋፍልና ጥላቻን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በጠቅላላው የሕዝቡን አንድነት ለማፍረስና ለማዳከም የታቀደ ስለሆነ ሕዝቡ ይህንኑ አውቆ ለአንድነቱ በይፋ እየታገለ ነው።

የኢሕአዴግ መመሪያ ጊዜው ያለፈበት የ‹ከፋፍለህ ግዛ› ፍልስፍና ስለሆነ፤ ብዙ ጉዳት ከማድረሱ አስቀድሞ የያንዳንዱን ግለሰብ መብት በሚያስከብር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት አለበት። ይህም አገሪቱን በዲሞክራሲያዊ ሥነ ሥርዓት ለማስተዳደር አስፈላጊ በሚሆን የክፍለ ሀገሮች አከፋፈል ወይም ታሪክንና የኢኮኖሚ ልማትን መሠረት በማድረግ በሚዘጋጅ መዋቅር ቢሆን ይመረጣል። በቅርቡ ኢሕአዴግ በጎሣ ላይ በተመሠረተ አስተሳሰብ ያጸደቀው ካርታና የክፍለ ሀገሮች መዋቅር ሕገ ወጥ ነው። በመሠረቱ ግን አሁን ያለው የኢትዮጵያ የአስተዳደር ካርታ የሚለወጥበት ምክንያት አለ ለማለት አስቸጋሪ ነው።

ከታሪክ አንጻር ሲታይ፤ አማራው በሰሜን በኩል ካሉት ትግርኛ ተናጋሪዎች ወገኖቹ (ትግራይና ኤርትራ) ጋር በታሪክና በባሕል የተሣሠረ ስለሆነ፤ ለኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት በኅብረት ሲታገል ኖሯል።

ነገር ግን መንግሥቱ ኃ/ማርያም በትግራይና በኤርትራ ላይ የፈጸመውን ግፍ በጠቅላላ ከአማራው ሕዝብ እንደተሰነዘረ በማስመሰልና ገዢውን ክፍል ከተራውና ከተገዢው ሰፊ አማራ ሕዝብ ባለመለየት፤ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባርና የኤርትራ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር ተጠሪዎች ለብዙ ዘመናት በአማራውና በትግርኛ ተናጋሪው



ሕዝብ መካከል የቆየውን ወዳጅነት ለማሻከር ከፍተኛ ዘመቻ አድርገዋል፤ በማድረግም ላይ ይገኛሉ። ሆኖም የትግራይና የኤርትራ ሕዝብ በገዢውና በተገዢው መደብ መካከል ያለውን ልዩነት ስለሚያውቅ በጠቅላላው በአማራው ላይ የሚሰበከውን የጥላቻ ዘመቻ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ዘመን እንዳልተቀበለው ሁሉ አሁንም እንደማይቀበለው በአዲስ አበባ፤ በለንደን፤ በዋሽንግተን፤ በሎስ አንጀለስ እንዲሁም በሌሎች አገሮች የሚደረጉ ትዕይንተ ሕዝቦች ይመሰክራሉ።

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አሥራ ሰባት ዓመታት በደል ሲፈጽም የቆየው መጠኑ ቢለያይም፤ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንጂ በተለይ በትግራይና በኤርትራ ሕዝብ ላይ ብቻ አልነበረም። የተፈጸመው በደል ለነፃነት የሚደረገውን ትግል አፋፋመው እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት አላፈረሰውም። የመከራውን ጽዋ ሁሉም አብረው ቀምሰዋል። ይህን እውነት ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን።

መንግሥቱ ኃ/ማርያም ባገራችን ላይ ከመጠን በላይ የሆነ መከራና ሥቃይ ለአሥራ ሰባት ዓመት ሲፈጽም ከቆየ በኋላ፤ መሰሎቹ ጀርመኑ ሂትለር፤ ኢጣልያዊው ሙሶሊኒ፤ ኡጋንዳው ኢዲ አሚን ጊዜያቸው ሲደርስ እንደተደመሰሱ ሁሉ እርሱም ከኢትዮጵያ ገጸ ምድር በኖ ጠፍቷል። በኢትዮጵያም ታሪክ ውስጥ እንደ ከፍተኛ አረመኔና አገር አጥፊ ሲታወስ ይኖራል። ተተኪ መሪዎች ሕዝብ የሰለቸውን የነቀፌታ ዘመቻን ጋብ አድርገው የሰላም ዘመቻን ካልጀመሩ የሕዝብ ቅሬታ መንግሥቱን ፈንቅሉ እንደጣለው ሁሉ እነርሱንም ይተፋቸዋል።

የመላ ኢትዮጵያውያን የጋራ ጠላት ከተወገደ በኋላ በአገራችን ላይ ምን ዓይነት አስተዳደር ሊመሰረት ይገባል? ለልዩ ልዩ ብሔረሰብ ጉዳዮችስ ምን መፍትሔ ይሰጣል? የመሬት ይዞታ በምን ዓይነት ይመራል? በነዚህና በሌሎችም አገር ነክ ጉዳዮች ላይ በችኮላና በስሜት በመመራት እርምጃ ከመውሰድ፤ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተውን ሕዝብ ሐሳብ መጠየቅና በሕዝቡ ፍላጎት መሠረት አስፈላጊውን ውሳኔ ማድረግ ተገቢ በሆነ ነበር። ይህን ለማሟላትም እንኳ ያሁኑ መንግሥት ጊዜያዊ ስለሆነ የሚተካው መንግሥት በሕዝብ ተመርጦ የሚያጠናቅቀው ተግባር ነው።

ነገር ግን የኢሕአዴግ አሠራር ‹እኔ አውቅልሃለሁ› ያለውን የደርግን ስልት የተከተለ ሆኖ እናየዋለን።

ለምሳሌ

(1) ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. በሐምሌ ወር 1983 ዓ.ም. አዲስ አበባ የጸደቀው ቻርተርና በሱ መሠረት የተሰየመው ባለ 87 የተወካዮች ምክር ቤት፣ በኢሠፓ ስም መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የራሱን ደጋፊዎች እንደሰበሰበ ሁሉ ኢሕአዴግ ለራሱ ዓላማ እንደሚስማማ አድርጎ ያቀነባበረው ምክር ቤት አባላት አመራረጥ ከኢሠፓ አባላት አመራረጥ በምንም ስለማይለይ፣ የምክር ቤቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ አይወክልም። (Africa Confidential, July 1991)

(2) ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከ33-35% የሚሆነው አማራ አልተወከለም (IMBYLTA, vol. 1, no.3/4 p.5)፣ ኢሕአዴግ አማሮች ናቸው ብሎ ለናሙና የመረጣቸው፣ አማራው ሕዝብ ስለማያውቃቸውና የውክልናም ሥልጣን ስላልሰጣቸው አይወክሉትም።

(3) ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳችም ውክልና ሳይሰጣቸው - ጊዜያዊ አቅዋም እንኳን ሳይኖራቸው - የኢሕአዴግና የኢሕነአግ ተጠሪዎች ስለ ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል የተፈራረሙት ስምምነት ሕገ ወጥ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞውን ደጋግሞ እያሰማ ነው። በታሪክ ዘንድም ያስጠይቃል። ከዚህም አልፎ ሐገሪቱን በጎሣ ለመከፋፈል የሚደረገው እሽቅድድም ኢሐአዴግ ስለ ኤርትራ የወሰደውን እርምጃ ለማጠናከር መሆኑ ግልጽ ነው።

አማራው ሕዝብ የአመጣጡን ታሪክና ምንጭ ባይዘነጋም፣ ከምንጩ ይልቅ ኢትዮጵያዊነቱን ሲያስቀድምና ሲያጎላ ይታያል። ስለሆነም፣ ኢትዮጵያዊነትን ማስቀደም ወይም አጉልቶ ማሳየት አማራነትን መካድ ወይም የለም ማለት አይደለም። አማራም መሆን በአሁኑ ጊዜ ከዘር አልፎ ወደ ቋንቋና ሥልጣኔ ደረጃ የተዛወረ ይመስላል።

በዘርና በጎሣ ፍልስፍና በሚያምኑና ለዘርና ለጎሣ ቅድሚያ በሚሰጡ ሰዎች ዘንድ አማራው ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱን በማስቀደሙ ምክንያት ‹አማራ የለም› ማለታቸው ፍጹም ስሕተት ነው። ጎሣን ማስቀደም ኢትዮጵያዊነትን እንደማይሽር፣ ኢትዮጵያዊነትን ማስቀደም አማራነትን አይሽርም፣ አይደመስስም። አማራው ኢትዮጵያን ከሰባት መቶ ዓመታት በላይ ሌሎቹን ጎሣዎች ሁሉ ሲያስተባብር የቆየ እንደመሆኑ መጠን፣ ከልዩ መታወቂያው (ከአማራነት) ይልቅ በዋና መታወቂያው (በኢትዮጵያዊነት) መጠራትን ይመርጣል።



የሌለ መምረጥ ስለማይችል፣ ይህ ለአማራ ሕልውና ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

ለመሆኑ አንድን ሰው አማራ፣ ኦሮሞ ወዘተ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ዘር ነውን? ከሆነስ፣ ድብልቅ ጋብቻ ሲኖር ስንት መቶኛው ደም ነው ዘርን የሚወስነው?

ቋንቋ ነውን? የማን ቋንቋ? የወላጆች? ከወላጆች ያንዱ? የየትኛው? ወይስ የአካባቢ?

ወይስ ሥልጣኔ? የማን? የናት ወይስ ያባት? ወይስ የተወለዱበት ስፍራ? የትውልድ ቦታ እውጭ አገር ቢሆንስ?

ይህ ሁሉ በዘር ጉዳይ መራቀቅ፣ በአገራችን ውስጥ ላለው ችግር መፍትሔ አይሆንም። የጎሣ ሐረግ መጥቀስ ወይም የእገሌ ጎሣ ወገን ነኝ› ማለት ታሪክ በመጥቀስ ለማስታወስ ካልሆነ በስተቀር ፋይዳም የለው፣ እንዲያው በደፈናው ጠባብ ጎሣዊነትና ብሔረተኛነት ነው። ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የሁሉም የወል መታወቂያ የሆነው ኢትዮጵያዊነት ነው።

አማራው በአስተዳደር ተካፋይ ሆኖ ባገኘው ትምህርት ምክንያት፣ ሰፋ ያለ የሥራ ልምድ ያለው ስለሆነ፣ ከሁሉም የኢትዮጵያ ጎሣዎች ጋር በተለይም ከትግሬው፣ ከኦሮሞው፣ ከጉራጌው በጋብቻ ተቀላቅሏል ተሳስሯል፣ በአኗኗርም ተቀላቅሏል። ስለዚህ ዛሬ አማራ ስንል ከማንም ጋር ያልተቀላቀለ (ያልተከለሰ) ንጹሕ የቤተ አምሐራ ተወላጅ ማለታችን ሳይሆን፣ ከአማራ ወላጅ (ወይም ወላጆች) የተወለደ፣ አማርኛ የሚናገር፣ የአማራን ሥነ ሥርአት የተከተለና ማንነቱን የሚያውቅ (‹Identity Crisis› የሌለው) ማለታችን ነው። በሌላ አነጋገር፣ አንድ ሰው አማርኛ በማይነገርበት ሥፍራ ተወልዶ ሌላ ቋንቋና ሥነ ሥርዓት ይዞ ቢያድግ፣ የዘሩን ሐረግ በመቁጠር (የጠፍ ቅንጣት ያህል እንኳን ብትሆን) አማራ፣ ኦሮሞ ወዘተ ነኝ የማለት መብት አለው። ይህም ከሮማውያን የሕግ ፍልስፍና ጋር ከሚስማማው ከኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥትና ፍትሐ ብሔር ሕግ አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰላል። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ያንድ ሰው ማንነት ማለት ጎሣ፣ ዘርና ዜግነት የሚወሰነው በወላጆች ማንነት ነው። በአንግሎ-ሳክሰን የሕግ አስተሳሰብ ደግሞ ያንድ ሰው ማንነት የሚወሰነው በተወለደበት ስፍራ (አገር) መሠረት ነው። ለምሳሌ ከኢትዮጵያውያን ወላጆች

አሜሪካን አገር የተወለደ ሕፃን አሜሪካዊ ይሆናል።

ባሁኑ ጊዜ በመንግሥት ደረጃ የሚካሔደው በጎሣ ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ ካልቀረና የያንዳንዱን ግለሰብ መብት የሚያስከብር ሕገ መንግሥት ተቀርጾ በነፃ ምርጫ ላይ የተመሠረተ መንግሥት ካልተፈጠረ፣ ኢትዮጵያ የበለጠ አስጊ ሁኔታ ላይ ትወድቃለች።

ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ የሚያስፈልጋት የአስተዳደር ሥርዓት ስለ ሰው ልጅ መብት እ፣አ፣አ፣ በ1948 በተባበሩት መንግሥታት በወጣው ሕግ መሠረት የእምነት፣ ሐሳብን የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብና የመቃወም ነፃነት፣ እንዲሁም ንብረት አፍርቶ የመጠቀም፣ እኩልነት፣ ወንድማማችነትና እህትማማችነት በጠቅላላው የሕግ የበላይ ገዢነት በተግባር የሰፈነበትና ሕዝቡ በሚገባ የሚሳተፍበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። ጊዜያዊው መንግሥት ግን ‹እኔ አውቃለሁ› በማለት ሕዝቡ ሳይወክለው አገሪቱን እየከፋፈለ የማዕከላዊ መንግሥትን ሥልጣን እያጠፋ፣ ሕጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎችን መስጠቱ የዲሞክራሲ በር በኢትዮጵያ ቀስ በቀስ እየተዘጋ መምጣቱን ስለሚጠቁም እጅግ የሚያሰጋ ነው።

# ክፍል ስድስት

## መደምደሚያ

ከዚህ በላይ በተደረገው ምርምር ‹አማራ› የሚባል ዘር ወይም ነገድ የለም ለሚለው ክርክር፣ አማራ መኖር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያንም ዕድል ከሰባት መቶ ዘመናት በላይ አማራ ያልሆኑትን ሁሉ ለአንድ ዓላማ (ያገራችንን አንድነትና ነፃነት ለመጠበቅ) በማስተባበር ሲመራ የቆየ መሆኑን በሦስት የኢትዮጵያ ታሪክ ምዕራፎች - የግራኝ አሕመድ ወረራ፣ የዐድዋ ጦርነት፣ እና የ1928 ዓ.ም. የኢጣልያ ወረራ - አማካይነት በመጠኑም ቢሆን ለማስረዳት ሙከራ ተደርጓል። ይህም በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ሐቅ ስለሆነ፣ ተረት ወይም ልብ ወለድ ታሪክ አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪክ ሐረግ ተሳስሮ፣ የሀገሩን አንድነትና ነፃነት በኅብረት ጠብቆ፣ እርስ በርሱ ተጋብቶና ተዋልዶ፣ በንግድና በልዩ ልዩ ተግባር ተሰማርቶ፣ የክፍለ



ሀገር ወሰንና ርቀት ሳያግደው የይለፍ ማስረጃ ሳያስፈልገው በነፃነቱ ኮርቶ፣ በሰላም ሰርቶ የሚኖር ሕዝብ ሲሆን ዛሬ ይህ በኅብረት ላይ የተመሰረተው ኑሮው እንዲቃወስ፣ ጠባብ በሆነ የጎሣ ደረጃ እንዲያስብና እንዲኖር የሽግግሩ መንግሥት መመሪያ መሆኑ እጅግ ያሳዝናል።

የፖለቲካ ሥልጣን የጠማቸው አንዳንድ ሰዎች ሌላ መንገድ ሲያጡ በጐሣ ላይ የተመሠረተ ፍልስፍናን መመሪያቸው ያደርጉታል። ኢትዮጵያ ዱሮ ሳይሆን ዛሬ የተፈጠረች በማስመሰል ታሪክን እያዛቡ አንዱን ጎሣ ከሌላ በማጋጨት በአርሲ በሐረርጌ የነውሐን ሽማግሌዎች፣ ሴቶች፣ ሕፃናት ደም መፍሰሱ አሳዛኝ ዜና ነው። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ መዘዋወር አለመቻሉም የሀገሪቱ አንድነት አዳጋች ደረጃ ላይ መድረሱን ያመለክታል።

ደካማ መሪ ከፋፍሎ በመግዛት ዘዴ መጠቀም ይፈልግ ይሆናል፣ በአጭሩ ይቀጫል፣ ሕዝብም ታሪክም ይተፋዋል። ብልህ መሪ ግን ሕዝብ የሚግባባበትን ዘዴ ይቀይሳል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ በሽማግሌዎች ምክር አያሌ ንትርኮችን፣ የውስጥ ግጭቶችን ለማስወገድ ጋዜጦቻችን አትተውበታል። አግባብ ያለው የታሪክ ምሳሌ መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል። አማራና ኦሮሞን መለያየት መሳ ለመሳ የተደባለቀ ጥቁርና ነጭ ጤፍን ለመለያየት እንደመሞከር ነው ያሉትን የአንዳንዶቻችን ጓደኞች አያት የነበሩትን አባ ዶዮን ማስታወሱ አግባብ አለው። በምዕራብ ኢትዮጵያም በኢጣልያ ወረራ ዘመን በኢጣልያ ፕሮፓጋንዳ መሠረት አማራውን ለመጨረስ የተነሳሳውን ኦሮሞ ‹ምን ስላደረገህ ነው› በማለት ድርጊቱን በመቃወም አገራቸውን ለቅቀው ከምዕራብ ኢትዮጵያ ወደ ሱዳን የተሰደዱትን ብላታ ዴሬሳን፣ ‹እኔን ሳትገድል አማራን አትገድልም› ብለው በመመከት ከበር ላይ በመጋፈጥ ኦሮሞውን የመለሱትን የከፋውን አባጅፋርን ታሪክ ከአባቶቻችን ግሀደር መረዳቱ ኢትዮጵያ በፍቅር የተሳሰሩ ሕዝቦች የኖሩባት አገር እንደነበረች ያስተምረናል።

የነዚህን የአባቶቻችን የአንድነት ስሜት የተከተሉ ከኦሮሞው ከትግሬው ከአማራው ከኤርትራዊው ከሌሎቹም ብሔረሰቦች የተውጣጡ ግለሰቦች የኢትዮጵያን ሕልውና ለማስጠበቅ የሚቻልበትን ዘዴ ለማስፈን፣ በብሔረሰብ ስም የተሟረውን እሳት ለማጥፋት ተደራጅተዋል። የአብዛኛውን የአዲስ አበባ ሕዝብ ድጋፍ ማግኘታቸው በግልጽ እየታየ ነው። የመዘዋወር ዕድል ቢሰጣቸው ተመሳሳይ ድጋፍ በመላ

ኢትዮጵያ የማያገኙበት ምክንያት አይኖርም። በስደት ላይ ለምንገኝ ዲሞክራሲን በሥራ ላይ ለምንመለከት ኢትዮጵያውያን የነዚህ ግለሰቦች መደራጀት መልካም የነፃነት ብልጭታ መኖሩን ያመለክተናል።

ከፍ ብሎ እንደተገለጠው ለአገራችን ችግር መፍትሔ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያጸድቀው ሕገ መንግሥት መሠረት መሠረታውያን የሰው ልጆች መብቶች ሲከበሩ፣ ክፍለ ሀገሮች የየራሳቸው የውስጥ አስተዳደር መብት ሲኖራቸው፣ እኩልነት ትክክለኛ ፍርድ በጠቅላላው በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ሲሰፍንና የሕግ የበላይ ገዢነት በተግባር ሲረጋገጥ ነው። በዘርና በጎሣ ሳይሆን፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ዓላማቸው ተወዳድረው አሸናፊ የሆኑ የፖለቲካ ቡድኖች መሪ ሲሆኑ ሰላም፣ መረጋጋትና ብልጽግና ይገኛል። ይህ ሲሆን፣ ዘር ወይም ጎሣ የታሪክ ማስታወሻ እንጂ የፖለቲካ ወይም አስተዳደር ፍልስፍና አይሆንም። ያች ቀን ሩቅ እንደማትሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ ተስፋ ነው!!



## ዋቢ መጻሕፍትና ድርሰቶች


1. መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ በአለቃ ኪዳነ ወልድ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1948 ዓ.ም.
2. ከማቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1951 ዓ.ም.
3. የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ ከአለቃ ታየ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1964 ዓ.ም
4. የጎራኝ አህመድ ወረራ፣ በተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1966 ዓ.ም.
5. የኢትዮጵያ ታሪክ (ኑብያ አክሱም ዛጔ) ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ 1951 ዓ.ም.
6. የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣
   ሀ) ከአጼ ይኩኖ አምላክ እስከ አጼ ልብነ ድንግል ሁለተኛ እትም፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1966 ዓ.ም.
   ለ) ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1953 ዓ.ም.
   ሐ) ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ አራተኛ እትም፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1946 ዓ.ም.
7. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣
   ሀ) አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1981 ዓ.ም.
   ለ) አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1982 ዓ.ም.
   ሐ) አጼ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983 ዓ.ም.
8. የኢትዮጵያ ታሪክ በ16ኛው ክፍለ ዘመን፣ ይልማ ዴሬሳ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም.

9. The Survival of Ethiopian Independence, Sven Rubenson, London, Heineman, 1978
10. Ethiopia: A Pawn in European Diplomacy History, Ernest Work, New York, The Mc Millan Company, 1935.
11. Trimingham, J.Spencer Islam in

Ethiopia, Oxford University Press, 1952.
12. The Lost Empire, Philip Caraman, University of Notre Dame Press, 1990.
13. The Life and Times of Menilik II H. Marcus, Oxford Clarendon Press, 1975.
14. Wax and Gold, Donald N.Levine, University of Chicago Press, Chicago, 1972
15. A History of Ethiopia, A.H.M Jones, Oxford, Clarendon Press, 1955.
16. Ethiopia at Bay, John H. Spencer, Reference Publications Inc, 1987.
17. The Unity and Territorial Integrity of Ethiopia, Getachew Haile, The Journal of Modern African Studies 24, 3 (1986), pp 486-487
18. Semitic Languages Encyclopaedia Judaica, 4th edition, 1973, Jerusalem.
19. The Political Economy of Ethiopia, Edited by Marina Ottoway, Chapter 12 on Revolution, Nationality and the Ethiopian State by Christopher Clapham (pp 221-231), Praeger, New York, London, 1990
20. Transformation and Continuity in Revolutionary Ethiopia, Christopher Clapham, 1988
21. Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society, Donald N. Levine, Chicago and London, University of Chicago Press, 1974.